በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ

የአርማደጋ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ የወሰን ድንበር የክለላ ሪፖርት

ጥር 2004 ዓም

ባህር ዳር

ማውጫ

1. መግቢያ 4
1.1. አጠቃላይ ሁኔታ 4
በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚገኙ ዋና ዋና ዕፅዋት 4
በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚገኙ ዋና ዋና አጥቢ እንስሳት 5
2. የድንበር ወሰን ክለላው ዓላማ 7
3. የድንበር ወሰን ክለላው የአሰራር ስልት 7
4. የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት 8
4.1. የክለላውን ስራ ለማከናወን ኮሚቴ ማቋቋም 8
4.2. የታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ዳር ድንበር መከለል 8
4.3. የታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን የብዝሃ ህይወት ሃብት 11
የአውደጥናቱ ተሳታፊዎች 11
ከአውደጥናቱ የተገኘ ውጤት 12
በአውደ ጥናቱ የተደረሰበት የመግባቢያ ሀሳብ 12
5. በስራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች 13
5.1. ያጋጠሙ ችግሮች 13
5.2. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች 14
6. ወደፊት መከናወን ያለባቸው ስራዎች 14
7. የአጋር አካላትን ተሳትፎ፣ ተግባራትና ኃላፊነቶች 15
7.1. የክልል፣ ዞንና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ሴክተር 15
7.2. የክልል፣ ዞንና ወረዳ መስተዳደር ሴክተር 16
7.3. ክልል፣ ዞንና ወረዳ ግብርና ሴክተር 16
7.4. ክልል፣ ዞንና ወረዳ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሴክተር 17
7.5. ክልል፣ ዞንና ወረዳ አስተዳደር ፀጥታ ሴክተር 17
7.6. ክልል፣ ዞንና ወረዳ ፍትህ ሴክተር 17
7.7. ክልል፣ ዞንና ወረዳ ጤና ሴክተር 17
7.8. የሰሜን ጎንደር ዞን የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና አጠቃቀም ፕሮግራም 17
8. ዕዝል 18
8.1. የፀደቀ የቀበሌ የክለላ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ 18
8.2. ለጥበቃ ሠራተኞች መኖሪያ ቤት መስሪያ የተመረጡ ቦታዎች 26
8.3. ጥበቅ ስፍራውን በአዋጅ ለማቋቋም የተመረጡ ጉልቶች 26
8.4. በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የፀደቀ የአዋሳኝ ቀበሌዎች የድንበር ወሰን መረጃ 31

ምስጋና

የአርማደጋ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ የድንበር ክለላ ሲካሄድ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት በዋልድባ ገዳም ህግና ስርዓት ጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፍና በደኑና በህብረተሰቡ መካከል ጤናማ ግንኙነት እንዲኖር ለማድረግ ታስቦ ሲሆን ስራውም ከፍተኛ ትዕግስትና ኃላፊነት እንደሚጠይቅ ግልፅ ነው፡፡ ቦታው በአቀማመጡ ወጣ ገባና ተራራማ እንዲሁም ሞቃታማ በመሆኑ ስራው ረጅም ጊዜና ከፍተኛ ጉልበት የሚጠይቅ ነበር፡፡

ደኑ በተፈጥሮው በወንዞች ተከልሎ ለዓመታት በገዳሙ ህግና ስርዓት ከእርሻና ከሰፈራ ነፃ ሆኖ የኖረ ቢሆንም በአዋሳኝ ቀበሌዎች ከሚኖረው ማህበረሰብ ጋር ከቤት እንስሳት ግጦሽ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ትስስር አለው፡፡ በመሆኑም ከህብረተሰብ ተወካዮች ጋር በመወያየትና በመተማመን በክለላው ላይ የጋራ ስምምነት ላይ ለመድረስ ከፍተኛ ትዕግስትና ጥረት የጠየቀ ነበር፡፡

የድንበር ወሰን ክለላውን ስኬታማ ለማድረግ ከክልል ባህል፣ ቱሪምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ከተላከነው ሁለት ባለሙያዎች ጋር በመሆን ወሳኝና ከፍተኛ ስራ ለሰሩት ለአዲአርቃይ ወረዳ መስተዳደር፣ አስተዳደር ፀጥታ፣ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ ፖሊስ፣ ባህልና ቱሪዝም እና እንዲሁም የሌሎች ሴክተር መ/ቤት ኃላፊዎችና በኮሚቴ አባልነት በክለላው ላይ ለተሳተፉ ባለሙያዎች በቢሮው ስም የዚህ ሪፖርት አቅራቢዎች ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን፡፡

የድንበር ወሰን ክለላው ኮሚቴ አባላት

1. አቶ ሙሉጌታ አስናቀው የአዲአርቃይ ወረዳ አስተዳደርና ፀጥታ ጽ/ቤት ኃላፊ.....ሰብሳቢ
2. አቶ ኃብታሙ አደም የአዲአርቃይ ወረዳ አካባቢ ጥ/መ/አ/አ ጽ/ቤት ባለሙያ.....ፀሐፊ
3. አቶ ዮሐንስ መኩሪያው የባህል፣ ቱሪምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ባለሙያ.....አባል
4. አቶ በልስቲ ፈጠነ የባህል፣ ቱሪምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ባለሙያ.....አባል
5. ሳጅን አሰፋ ቆስቁሴ የአዲአርቃይ ወረዳ ፖሊስ ጽ/ቤት ባለሙያ.....አባል
6. የአዋሳኝ ቀበሌዎች አመራርና የህዝብ ተወካዮች.....አባል

1. መግቢያ

1.1. አጠቃላይ ሁኔታ

አርማደጋ የተፈጥሮ ደን በሰሜን ጎንደር ዞን በአዲአርቃይ ወረዳ ወስጥ የሚገኝ ሲሆን ጠቅላላ ስፋቱም 27852.8 ሄ/ር እንደሚደርስ ከጥናቱ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል።


አርማደጋ በአዲአርቃይ ወረዳ (አማራ ክልል) እና በማይፀብሪ ወረዳ (ትግራይ ክልል) መካከል ይገኛል። አጠቃላይ ቦታው ከአማራ ክልል የሰቋርና የዳልሻ ኪዳነ ምህረት እንዲሁም ከትግራይ ክልል የአብረታንት መድኃኒዓለም ገዳማትን ጨምሮ በዋልድባ ገዳም ስም ከ5ተኛው መቶ ክ/ዘመን ጀምሮ ለዘመናት ተከብሮ የኖረ የተፈጥሮ ደን ነው።

በአዲአርቃይ ወረዳ በኩል ከ5 ቀበሌዎች (በሰሜን ከአዲአረጋይ ቀበሌና ትግራይ ክልል፣ በምዕራብ ከነብራና ፍድቃ እና አለ. ቀበሌዎች፣ በምስራቅ ከአዲአረጋይና በርማሪያም ቀበሌዎች፣ በደቡብ ከበርማርያምና ጨውበር ቀበሌዎች) ጋር በቀጥታ የሚዋሰን ሲሆን ጠቅላላ ደኑ በተፈጥሮ በ3 ትላልቅ ወንዞች (እንስያ፣ ዛሪማና እንዞ) ተከልሎ ይገኛል። ይህ ቦታ ከዓለ. ቀበሌ ድቅቆና ዛሪማ ወንዞች መጋጠመያ እስከ ከጨውበር ቀበሌ (አጠላ አካባቢ) እና በርማሪያም ቀበሌ (የእንዞ ወንዝን ተከትሎ) በግምት ከ13^{0}19’55” እስከ 13^{0}29’40" ሰሜን ላቲቲዩድና ከ37^{0}49’03" እስከ 37^{0}59’16” ምስራቅ ሎንግቲውድ ላይ ይገኛል።

የአርማደጋ የተፈጥሮ ደን ከባህር ወለል በላይ ከ860 ሜ (የድቅቆና ዘሪማ ወንዞች መጋጠሚያ ዓለ. ቀበሌ) እስከ 1767 ሜ (በተፈጥሮ ደኑ መሃል ስውር እና በጨውበር ቀበሌ ወደ አጠላ አካባቢ) ክፍታ ድረስ በተፈጥሮ ደኑ ውስጥ ያለውን ሜዳማ፣ተራራማና ወጣገባ የደን መሬት የሚያጠቃልል ቦታ ሲሆን አብዛኛው የደኑ ክፍል በቆላ ስነ ምህዳራዊ ቀጠና (95%) የሚገኝ እና በርካታ ጠቀሜታ ያላቸውን እንስሳትና ዕፅዋት የያዘ ነው።

በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚገኙ ዋና ዋና ዕፅዋት

1. ሰርኪን*(Diospyros mespiliformis)*
2. ዶቅማ (*Syzygium guineese*)
3. ዋርካ (*Ficus vasta*)
4. ጥቁር እንጨት *(Prunus africana)*
5. ሾላ *(Ficus sur)*
6. ኩመል *(Mimusops kummel)*
7. ዞቢ *(Dalbergia melanoxylon)*
8. የቆላ ዋንዛ*(Piliostignia thonningii*)
9. የዕጣን ዛፍ(*Boswellia papyrifera)*
10. ሽመል *(Oxytenanthera abyssinica)*
11. ባምባ *(Ficus sycomorus)*
12. ክርክራ *(Anogeissus leiocarpus)*
13. አባሎ *(Combrefum molle)*
14. አንቋ *(Commiphora Africana)*
15. ኮርች *(Erythrina abyssinica)*
16. ችብሃ *(Ficus thonningii)*
17. ዋንዛ *(Cordia africana)*
18. ኮመር *(Tamarindus indica)*
19. ወይባ *(Terminalia brownii)*
20. ዛና *(Streospermum kunthisnum)*
21. ዳርሌ *(Sterculia africana)*
22. ግራር *(Acacia spp.)*



ምስል 1. የአርማደጋ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራን የሚያሳይ ካርታ

በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚገኙ ዋና ዋና አጥቢ እንስሳት

1. ነብር *(Panthra pardus)*
2. የቆላ አጋዘን *(Tragelaphus imberbis)*
3. ውድንቢ *(Tragelaphus oryx)*
4. ተራ ቀበሮ *(Canis aureus)*
5. ተራ ድኩላ *(Tragelaphus scriptus)*
6. ጉሬዛ *(Colobus abyssinicus)*
7. ጥሪኝ (*Civettics civetta*)
8. ሚዳቋ (*Sylvicapra grimmia*)
9. ሽልምልም ጅብ *(Hyaena hyaena)*
10. ተራ ጅብ (*Crocuta crocuta)*
11. ተራ ዝንጅሮ (*Papio Anubis*)
12. ክርክሮ (*Phacochoerus aethiopicus*)
13. የዱር ዓሳማ (*Sus scrofa)*
14. መጎዛ/አራጅ (*Mellivora capensis*)
15. ሽኮኮ (*Procavia capensis*)
16. ዳልጋ አንበሳ (*Caracal caracal*)
17. ሰሳ (*Oreotragus oreotragus*)
18. አነር (*Felis serval*)
19. ጃርት (*Hystrix cristata*)
20. ጦጣ (*Cercopithecus aethiops*)
21. ፌቆ (Ourebia ourebi)
22. አወልድጌሳ (*Orycteropus afer*)

በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው የሚገኙ ዋና ዋና አእዋፋት

1. **ርኩም** (Abyssinian ground hornbill)
2. **ገደ** (Augur buzzard)
3. **ሳቢሳ** (Egret spp.)
4. **ጭልፊት** (Tawny eagle)
5. **ቆቅ** (Francolin spp.)
6. **ዝግራ** (Vulturine guineafowl)
7. **ጆቢራ** (Vulture spp)
8. **ቁራ** (Corvus spp.)
9. **ዳክዬ** (Egyptian goose)
10. **አንገተ ጥቁር ጨጭ** (Dark-headed oriole)
11. **ጋጋኖ እንጥልጥል የሌለው** (Ibis spp.)
12. **ርግብ** (Speckled pigeon)
13. **ስቶርክ** (Ciconia spp.)
14. **ደበኔ** (Streptopelia spp.)
15. **አሳ ወጊ** (Long-tailed Cormorant)
16. **ጉጉት** (Verreaux's Eagle Owl)
17. **ሄሮን** (Grey heron)
18. **ግንደ ቆርቁር** (Green wood hoopoe)

ትቂቶቹ ሲሆኑ በአጠቃላይ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ከ30 በላይ ታላላቅ አጥቢ የዱር እንስሳት፣ ከ102 በላይ አዕዋፋት፣ ከ112 በላይ የዕዕዋት ዝርያዎች፣ 3 የዓሳ፣ የተለያዩ ተሳቢና ተራማጅ ዝርያዎች እንዳሉ ቀደም ሲል የተደረገው ዝርዝር ጥናት ያመለክታል። ከዚህ በመነሳት የተፈጥሮ ደኑን ቀደም ሲል ሲጠበቅበት የነበረው የዋልድባ ገዳም ህግና ስርዓት ሳይሻራረፍ ወደ ጥብቅ ስፍራነት ለማሳደግ በአጎራባች ቀበሌዎች የሚኖረውን ህብረተሰብና የገዳሙን ማህበረሰብ ባሳተፈ ሁኔታ የድንበር ወሰን ክለላ ተካሂዷል።

የአርማደጋ የተፈጥሮ ደን ከፍታው ከ860 ሜ ጀምሮ እስከ 1800 ሜ እየጨመረ የሚሔድ በመሆኑ በውስጡ የተለያዩ መልከአምድራዊ ገፅታዎች አሉት። የዛሪማ፣ እንስያ፣ እንዞና ሌሎች በርካታ ገባር የሆኑ ወንዝና ሸለቆዎችን ተከትሎ የሚገኙ የውሃ ዳር ደኖችን (Evergreen Riverine Vegetation) የሚወክል ምቹጌ (Habitat) የያዙ ስፍራዎች ሜዳማና ተዳፋታማ ሲሆኑ እጅግ ማራኪ ናቸው። ማይቀላባዱ፣ ማይደራሆት፣ ግራርና ኩመር አምቦ፣ ጓል ዘሪማ፣ ደማ ባሪና ዶቅማ፣ ክሳድ አጋዘን፣ ስፍራ አባይ፣ ሰኮሊፍ፣ ዓዳማይ እና ከፊሮ ሜዳማና ተዳፋታማ ከሆኑ ቦታዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እነዚህ የደን አካባቢዎች የዕጣን ዛፍና ሽመልን ጨምሮ በውስጣቸው እጅግ በጣም ግዙፍና ዕድሜ ጠገብ የሆኑ ዛፎችን አቅፈው የያዙ በመሆናቸው ለዘቦታ ጥበቃ (In-situ Conservation) ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። ከሜዳማና ተደፋታማ ቦታዎች በተጨማሪም የተፈጥሮ ደኑ በአብዛኛው ለአይን ማራኪ በሆኑ የተለያዩ ሰንሰለታማ ተራራዎች የተሞላ ሲሆን በውስጡም በዋናነት ኮምብረተም-ተርሚናልያ ውድላንድ ስርዓተ ምህዳርን (Combretum-Terminalia Woodland Ecosystem) የሚወክል የተፈጥሮ ደን ይገኛል። የአካባቢውን ስነ ምህዳር ለመጠበቅ ጉልህ አስተዋፅዖ ያለው የደኑ ሽፋን በአካባቢው ያልተዛባ ዝናብና መቀት እንዲሁም የተስተካከሉ ወቅቶች እንዲኖሩ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው ይታመናል። በስርዓተ ምህዳር ይዙቱ ደኑና የአካባቢው ማህበረሰብ ተደጋግፈው የሚኖሩ ሲሆን ለዓመታት በእሳት ቃጠሎ፣ ልቅ ግጦሽ (ቅራት)፣ ህገ ወጥ የዱር እንስሳት አደንና ደን ጭፍጨፋ እና እንዲሁም በተፈጥሮ ደኑ ውስጥ በሚካሄደው ዘላቂ ያልሆነ የዕጣን ምርትና አጠቃቀም ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት ይገኛል። ይህ ተፈጥሮዊ ይዘት ያለው የተፈጥሮ ደን በገዳሙ ስርዓትና ህግ

መሰረት ዘላቂ በሆነ ጥበቃና አጠቃቀም ተጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፍ በጥብቅ ስፍራነት ተከልሎ ለብዙሃ ህይወት ጥበቃ መዋል እንዳለበት ያሳያል፡፡

2. የድንበር ወሰን ክለላው ዓላማ

የድንበር ወሰን ክለላው የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፡-

- የአርማደጋ የተፈጥሮ ደን የብዝሃ ህይወት ሃብት፣ ተፈጥሮዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መስህብ ሃብቶች ለመጠበቅና ለማልማት እንዲሁም ወደ ጥብቅ ስፍራነት ለማምጣት እንዲቻል የአካባቢውን ማህበረሰብ ባሳተፈ መንገድ የዳር ድንበር ክለላ ማካሄድ (የታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ድንበርና ስፋቱን ለመወሰን)፣
- ለአጋር አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በማዘጋጀት ስለአካባቢው ግንዛቤ ለመፍጠር እና ስለአጠባበቁ የጋራ ግንዛቤ ለመያዝ፣
- ህጋዊ ዕውቅና ለማስገኘት የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣
- የአካባቢውን ማህበረሰብና ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ጤናማ ግንኙነት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣
- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ውስጥ የሚገኘውን ብዝሃ ህይወት ለመጠበቅና ለማልማት፣

3. የድንበር ወሰን ክለላው የአሰራር ስልት

- ለሚመለከታቸው አጋር አካላት (አስተዳደር፣ ግብርና ልማት፣ አካባቢ ጥበቃ፣ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች) የክለላውን ዓላማና ሂደት ማስተዋወቅና የትብብር ደብዳቤ ማስፃፍ፣
- ለወረዳ አስተዳደር፣ ግብርና ልማት፣ አካባቢ ጥበቃ፣ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤቶች የወሰን ድንበር ክለላውን ዓላማ ማስተዋወቅና ባለሙያ ማስመደብ፣
- የሚመለከታቸውን አጋር አካላት በመያዝ (አስተዳደር፣ ግብርና ልማት፣ አካባቢ ጥበቃ፣ ባህልና ቱሪዝም) ባለሙያዎችን፣ የቀበሌ አስተዳደሩን የአካባቢውን ህዝብና የሀይማኖት መሪዎችን የያዘ የድንበር ወሰን ከላይ ኮሚቴ ማቋቋም፣
- ትርፍ ጊዜን ጨምሮ በመጠቀም ከኮሚቴው ጋር በመሆን እና ደኑን ዙሪያውን በመዞር ክለላውን በቃለ-ጉበኤ በማስደገፍ ማካሄድ፣
- የጂፒኤስ ኮርዲኔቶችንና በደንብ የሚታወቁ ምልክቶችን መረጃ በመያዝ ከስምምነት ላይ መድረስ፣
- በአካባቢው ላይ ከአሁን በፊት የተሰበሰቡና የተጠኑ መረጃዎችን በመጠቀም ክለላውን ተግባራዊ ማድረግ፣
- በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ዙሪያ ለሚኖረው ህብረተሰብ የወሰን ደንበር ክለላውን ዓላማና ለወደፊት ጥብቅ ደኑ በጥብቅ ስፍራነት ቢጠበቅ የሚሰጠውን ጠቀሜታ በማስረዳት ግንዛቤ መፍጠር፣

- በአጎራባች ቀበሌዎች የሚኖረው ማህበረሰብ ተወካዮች በተገኙበት ወርክሾፕ በማዘጋጀት ከአጋር አካላት ጋር ምክክር ማካሄድ እና ስለክለላው የጋራ ግንዛቤ መያዝ፣

4. የተከናወኑ ዝርዝር ተግባራት

4.1. የክለላውን ስራ ለማከናወን ኮሚቴ ማቋቋም

ከክልል ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ፣ ከአዲአርቃይ ወረዳ አስተዳደር ፅጥታ፣ ፖሊስ (አስተዳደር ተወካይ)፣ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም እንዲሁም ከአዋሳኝ ቀበሌዎች የየቀበሌው ሊቀመንበርና ሌሎች የህዝብ ተወካዮችን ያካተተ የወሰን ድንበር ከላይ ኮሚቴ እንዲቋቋም ተደርጓል። የወሰን ድንበር ክለላውን የተሳካና በተቀላጠፈ መልክ እንዲከናወን ለማድረግ ጉዳዩ በይበልጥ የሚመለከታቸውን፣ ለረጅም ጊዜ በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ዙሪያ የኖሩ እና የአካባቢው ባላባቶች ተብለው የሚታወቁ፣ ስለአካባቢው በቂ ግንዛቤ ያላቸው ግለሰቦች በኮሚቴው ውስጥ እንዲካተቱ ተደርገዋል። በየቦታው የሚነሱ አስተዳደራዊ የህዝብ ችግሮችን ለመፍታት ከወረደው መስተዳደር አንድ አመራር እና አንድ ፖሊስ በቋሚነት ተመድበው ስራው እስኪጠናቀቅ ድረስ ስርተዋል። በተጨማሪም ከአዲአርቃይ ወረዳ የአካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለሙያ፣ ከየቀበሌዎች ደግሞ የተፈጥሮ ሃብት እና የአካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ባለሙያዎች፣ ርዕሳነ መምህራን፣ እንደ ቀበሌው ሁኔታ የእንስሳት ጤና እና የጤና ኤክስቴንሽን በለሙያዎች፣ የኮሚኒቲ ፖሊሶች፣ የቀበሌ ስራ አስኪያጅዎች፣ የሰበል ልማት ባለሙያዎች፣ የግብርና ሱፐርቫይዘሮች በአጠቃላይ ስራውን የሚከታተሉና ስለተፈጥሮ ደኑና አካባቢው በቂ መረጃ ያላቸው ባለሙያዎች በኮሚቴው ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል። በተጨማሪም ከየቀበሌዎቹ በመሬት ደልዳይ ኮሚቴነትና የሚፈጠሩ ችግሮችን በመፍታት በኩል በቂ ተሞክሮና መረጃ ያላቸው የቀበሌ አስተዳዳሪዎች፣ የመሬት ደልዳይ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች/አባል የነበሩ፣ የፍርድ ሸንጎ ሰብሳቢዎች፣ አፈ-ጉባዔዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ ከሰቋር እና ዳልሸሃ ኪዳነ ምህረት ገዳማት አባቶች/ተወካዮች፣ የብዙሃን ማህበራት ተወካዮች፣ ሚሊሻዎችና ኮማንደሮች በኮሚቴው በአባልነት ተካተዋል። በቀበሌ ደረጃ የተመረጡ ተወካዮች በታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አዋሳኝና ዙሪያ ከሚገኘው ህብረተሰብ ግልጽና ነፃ በሆነ ፈቃደኝነት የተመረጡ ናቸው።

4.2. የታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን ዳር ድንበር መከለል

የክለላ ስራው የተጀመረው በዓሊ ቀበሌ በኩል የዛሪማና ድቅቆ ወንዞች መደማምር (መገናኛ) ከሚባለው ቦታ ልዩ ስሙ የማህበረ ጅቡቲ የአትክልትና ፍራፍሬ አምራቾች እርሻ አጠገብ ከነጥብ አንድ በመነሳት የዛሪማ ወንዝን በመከተል እና ወደ ደኑ በማስገባት እስከ ዓሊና ሳንቅ ቀበሌ ድንበር ልዩ ስሙ ዳልሸሃ ኪዳነ ምህረት ገዳም

ሳሙኤል ቤ/ክርስቲያን አጠገብ ነጥብ አንድ መቶ አርባ ስምንት ድረስ ሲሆን በነብራ ፍድቃ ቀበሌ በኩል ደግሞ ከነብራ ፍድቃ እና ሳንቅ ቀበሌ ድንበር ልዩ ስሙ ጠረኩ እና ዛሪማ ወንዞች መጋጠሚያ (ከድልድዩ ዝቅ ብሎ) ከነጥብ አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ በመነሳት የዛሪማ፣ የአብዬ፣ ማይደንጎላ እና ሽልዋ ወንዝና ሸለቆዎችን በመከተልና ወደ ደኑ በማሰገባት እስከ ጨውበር እና ነብራ ፍድቃ ቀበሌ ደንበር ልዩ ሰሙ ነደላ አምባ ነጥብ ሶስመቶ ሰማኒያ ሶስት ድረስ ከዚያም በአዲአረጋይ ቀበሌ በኩል በመዞር አዲወፋሪ ቀበሌ (ማይፀብሪ ወረዳ) እና አዲአረጋይ ቀበሌ ድንበር ልዩ ስሙ አዲሃወልውል ማይቆላ ሸለቆ ከነጥብ ሶስመቶ ሰማኒያ አራት በመነሳት የእንስያን ወንዝ በመከተልና ወደ ደኑ በማሰገባት እስከ በርማሪያምና አዲአረጋይ ቀበሌ ድንበር ልዩ ስሙ የእንስያና እንዞ መገናኛ (መደማምርት ወይም ምድማር) ነጥብ አራት መቶ አራት ድረስ በመጨረሻም በበርማሪያም ቀበሌ በኩል ከነጥብ አራት መቶ አራት በመነሳት የእንዞን ወንዝ መከተልና ወደ ደኑ በማሰገባት እስከ ጨውበርና በርማሪያም ቀበሌ ድንበር ልዩ ስሙ የማይሸሃ እና እንዞ ወንዞች መገናኛ ነጥብ አራት መቶ ስድሳ ስምንት ድረስ ከዚያም ከነጥብ አራት መቶ ስድሳ ስምንት በመነሳት የማይሸሃን ሸለቆ በመከተልና ወደ ደኑ በማሰገባት እስከ ነደላ አምባ የጨውበር እና ነብራ ፍድቃ ቀበሌ ድረስ ያለው ቦታ የድንበር ወሰኑ ሳይለይ የክለላ ስራው ተጠናቋል።

የአዋሳኝ ቀበሌዎች የድንበር ወሰን ሲጠቃለል

1. **ዓሊ ቀበሌ፡-** የዛሪማና ድቅቆ ወንዞች መደማምር (መገናኛ) ከነጥብ 001 እስከ ሳሙኤል ቤ/ክርስቲያን ነጥብ 148፣
2. **ነብራ ፍድቃ ቀበሌ፡- ከ**ዳልሸሃ ኪዳነ ምህረት ገዳም (ከድልድዩ ዝቅ ብሎ) ከነጥብ 149 እስከ ነደላ አምባ ነጥብ 383፣
3. **አዲአረጋይ ቀበሌ፡-ከ**አዲሃወልውል ማይቆላ ሸለቆ ከነጥብ 384 እስከ የእንስያና እንዞ መገናኛ (መደማምርት ወይም ምድማር) ነጥብ 404፣
4. **በርማሪያም ቀበሌ፡-**ከነጥብ 404 እስከ የማይሸሃ እና እንዞ ወንዞች መገናኛ ነጥብ 468፣

የተፈጥሮ ደኑ አዋሳኝ በሆኑት 5 ቀበሌዎች ከጨውበር በስተቀር ከነጥብ 001 እስከ 468 ድረስ የተከለለ ሲሆን ከየቀበሌው በተመረጡ የኮሚቴ አባላት ስምምነት የተረጋገጠና የሁሉም ቀበሌዎች የክለላ ኮሚቴዎች አፅድቀው የላኩትን የስምምነት የውሳኔ ሰነድ የወረዳው ካብኔ ጉዳዩን አምኖበት ስምምነቱን አፅድቆታል።

ካቢኔው ስምምነቱን ሲያፀድቅ ለወደፊቱ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦች በዝርዝር ተለይው ከባለሙያዎችና ከካቢኔው አባላት ተገቢው ገለፃ ተተሰጥቶባቸው የክለላው ሂደትና አፈፃፀም ትክክል መሆኑን በማረጋገጥ ነው።

የተፈጥሮ ደኑ በተፈጥሮ በወንዞች ተከለለ በመሆኑና ከአጎራባች ቀበሌዎች ነዋሪ ማህበረሰብ እርሻ ጋር የድንበር ውዝግብ የሚያስነሳ ቦታ የሌለው በመሆኑ በየቀበሌው ከክለላው በፊት ከተመረጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ስለክለላው ጥቅምና ሂደት ውይይት በማድረግ፣ ሰምምነታችንን ቃለጉባኤ ይዞ በመፈራረምና በማፅደቅ ከዚያም በክለላው ሂደት ድንበሩን በማሳየትና የልዩ ቦታዎችን ስም በመናገር ተሳትፎ የሚያድርጉና ታዛቢ የሚሆኑ ግለሰቦችን በማስመረጥና በማስመደብ፣ በክለላው ወቅት ደግሞ ከወረዳና ከቀበሌ ተወካዮች ጋር በጋራ በመንቀሳቀስ እያንዳንዱን የድንበር ወሰን በመነጋገር፣ በመግባባትና የጋራ ግንዛቤ በመያዝ፣ የጅፒኤስ ኮርዲኔት ንባብ በመውሰድ፣ የድንበር ቁጥር በመስጠትና የወሰን ምልክት በማድረግ ተከናውኗል፡፡

ቀደም ሲል በተደረጉ ጥናቶች የተፈጥሮ ደኑ ልቅ ግጦሽ (ቅራት)፣ የሰደድ አሳት፣ ህገ ወጥ የዱር እንስሳት አደንና ደን ጭፍጨፋ እና እንዲሁም በተፈጥሮ ደኑ ውስጥ የሚካሄደው ዘላቂ ያልሆነ የዕጣን ምርትና አጠቃቀም ዋነኛ ችግሮች መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ ሌላ ደኑ ለረጅም ጊዜ ከሰፈራና ከእርሻ ንክኪ ነፃ ሆኖ የኖረ ሲሆን ወደፊትም ቦታው በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ለእርሻና ሰፈራ እንደማይፈለግ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አንፃር በክለላው ወቅት የእርሻ መሬቶችንም ሆነ መንደሮችን በተመለከተ ችግር የሚፈጥር ሁኔታ አልነበረም፡፡ የተፈጥሮ ደኑ በተፈጥሮው በወንዞች የተከበበ ሲሆን ያሉት የአርሻ መሬቶችም ሆነ መንደሮች ከተፈጥሮ ደን ክልሉ ውጭ የሚገኙ ናቸው፡፡ በመሆኑም የድንበር ወሰን ክለላላው በአብዛኛው መሰረት ያደረገው በተፈጥሮ ደኑ ላይ ያላውን ሰው ሰራሽ ጫና በመቀነስ፤ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት እንዳለ ጠብቆ በማቆየት፤ በደኑና በአካባቢው ማህበረሰብ ጤናማ ግንኙነት እንዲኖር ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ነው፡፡ የሁሉም አዋሳኝ ቀበሌዎች የድንበር ወሰን ክለላ ከተጠናቀቀ በኋላ በቀበሌ ደረጃ የፀደቀውን መነሻ በማድረግ የተያዘው ቃለጉባኤና የኮሚቴዎች የስምምነት ፊርማ የወረዳው ካብኔ ከተወያየበት በኋላ በወረዳው ካብኔ እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡በቀበሌና በወረዳ ደረጃ የፀደቀው የድንበር ወሰን የክለላ ሰነድ አንድ ኮፒ ለቀበሌው አስተዳደር፣ አንድ ኮፒ ለወረዳ አስተዳደር፣ አንድ ኮፒ ለወረዳ ግብርና ጽ/ቤት፣ አንድ ኮፒ ለወረዳው አካባቢ ጥ/መ/አ/አ/ ጽ/ቤት፣ ዋናው ኮፒ ደግሞ ለክልሉ ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

4.3. የታሳቢ ጥብቅ ስፍራውን የብዝሃ ህይወት ሃብት ተፈጥሮዊ ባህላዊና ታሪካዊ ሀብቶች ለመጠበቅና ለማልማት በአዋሳኝ ቀበሌዎች ለሚኖረው ህብረተሰብ ተወካዮች፣ ለዋልድባ ገዳም ተወካዮች እና ለወረዳና ዞን አጋር አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ የምክክር አውደ ጥናት ማካሄድ፣

የአውደጥናቱ ተሳታፊዎች

- **ከባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ፡-** የዱር እንስሳት ጥናት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም የስራ ሂደት ባለቤትና ባለሙያዎች፣ ከፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ደጋፊ የስራ ሂደት ፣
- **ከሰሜን ጐንደር ዞን፡-** ዞኑ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ፣ ግብርና መምሪያ፣ አካባቢ ጥ/መ/አ/አ/መምሪያ፣ ሰሜን ጐንደር ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አጠቃቀም ፕሮግራም፣ ቤተክህነት፣ አስተዳደር ፀጥታ፣ ጐንደር ዩኒቨርሲቲ፣ ኮሚኒኬሽ መምሪያ፣
- **ከአዳርቃይ ወረዳ፡-** የወረዳው የሴክተር ሃላፊዎችና ተወካዮች፣ የወረዳው ቤተክህነት ኃላፊዎችና ተወካዮች፣ ከታሳቢ ጥብቅ ስፍራው አጎራባች ቀበሌዎች አመራሮች፣ በህዝብ የተመረጡ የሃገር ሽማግሌዎችና የሃይማኖት መሪዎች እንዲሁም ከዳልሸሃ፣ ሰቋርና አብረንታንት ገዳማት አበምኔቶችና ተወካይ አባቶች የተገኙ ሲሆን ወንድ 53 ሴት 2 በድምሩ 55 ሰዎች ተሳትፈዋል፡፡

የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ክለላ ከተካሄደ በኋላ የደኑ አዋሳኝ ቀበሌዎች አመራሮችና የህብረተሰብ ተወካዮች፣ የዋልድባ ገደም ተወካዮችና የአጋር አካላት ተወካዮች በአጠቃላይ 55 ሰዎች በተገኙበት ጥር 6/2004 ዓ.ም አውደ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ለውይይቱ መነሻ ይሆን ዘንድም በአውደ ጥናቱ የሚከተሉት ርዕሶች ለተሳታፊው ቀርበዋል፡፡

1. ስለጥብቅ ስፍራዎች ምንነት፣ ጠቀሜታና አጠባበቅ እንዲሁም በሀገራችን ስላለው ተሞክሮ፣
2. በክልላችንና በሀገራችን ተግባራዊ እሆኑ ስላሉ የዱር እንስሳት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎች፣ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደንቦች፣
3. የአርማደጋ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ ያለው ተፈጥሮዊ፣ ታሪካዊና ኃይማኖታዊ ሃብቶች፣ ጥብቅ ስፍራ ለመሆን ያለው አቅም፣ ጥብቅ ስፍራ ቢሆን ያለው ጠቀሜታ እና በአሁኑ ወቅት ያሉበት ችግሮች (በአርማደጋ ደን ላይ ከተደረጉ የጥናትና የክለላ ስራዎች)፣
4. የአርማደጋ ታሳቢ ጥብቅ ስፍራ የክለላ ሪፖርትና የአጋር አካላት ሚና፣

በአራቱ ጉዳዮች ዙሪያ ለተሳታፊዎች በቢሮው ሰፊ ገለፃ ከተካሄደ በኋላ የሰሜን ጎንደር ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ አቶ በሪሁን እና የአዲአርቃ ወረዳ አስተዳዳሪ አቶ

ዳኘው ውይይቱን እንዲመሩት ተደርጎ በደኑ ጥበቃ ዙሪያ በተሳታፊዎች ጥልቅ ውይይት ተደርጓል፡፡ በውይይቱም በስፋት ከተነሱ ሃሳቦች መካከልም፡

1. ከዋልድባ ገዳም አባቶች አርማደጋ ‹‹ፓርክ›› መሆን የለበትም መንግስት ጣልቃ መግባት የለበትም ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን ደኑ በገዳሙ ህግና ስርዓት መጠበቅ ይችላል የሚለው ሃሳብ፣
2. ከቀበሌ አመራሮችና የህብረተሰብ ተወካዮች አርማደጋ በማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራነት ተፈርጆ በመንግስት እገዛ እንዲጠበቅ ነገር ግን ፓርክ መሆን እንደሌለበትና በተለይም የገዳሙን ህግና ስርዓት ሊፃረር ስለሚችል ቦታው ለቱሪዝም መዋል እንደሌለበት ይህ ከሆነ ግን አብዛኛው ህዝብ ሊቀበለው እንደማይችል ስለሆነም አጀንዳው ወደ ቀበሌ ወርዶ በኮንፈረንስ መልክ ህዝቡ መወያየትና መስማማት አለበት የሚለው ሃሳብ፣
3. መንግስት ከህብረተሰቡና ከገዳሙ ጋር በመተባበር ደኑን መጠበቅ አለበት ለዚህ ደግሞ ህብረተሰቡም ሆነ የገዳሙ አባቶች መስማማትና ፈቃደኝነታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው የሚለው ከመንግስትና ከአጋር አካላት ተወካዮች የቀረበው ሃሳብ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከአውደጥናቱ የተገኘ ውጤት

- ከላይ በተጠቀሱት ርእሶች ዙሪያ ግንዛቤ መፈጠሩ፣
- በአርማደጋ ላይ እየደረሱ ያሉ ጫናዎችን መረዳት መቻሉ፣
- በአርማደጋ ውስጥ ያሉ ጫናዎችን ለማስወገድ የሚያስችሉ መንገዶች መቀየሳቸው፣
- የአጋር አካላት ሚና መለየት መቻሉ፣
- በሀብቱ ጥበቃ ላይ በተወሰነ መልኩ መግባባት ላይ መደረሱ፣

በአውደ ጥናቱ የተደረሰበት የመግባቢያ ሀሳብ

የአርማደጋ የተፈጥሮ ደንን ከመጠበቅ ጋር ተያይዞ በየትኛው የጥበቃ ክፍል /category/ ውስጥ መቀመጥ አለበት በሚለው ጉዳይ ሃሳቦች የቀረቡ ሲሆን የዋልድባ ገዳም የማህበረሰብ ጥብቅ ደን መባል እንደሚኖርበት ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን ፓርክ የሚለውን ስም በአቅራቢያው ካለው የሰሜን ተራራዎች ብሄራዊ ፓርክ ጋር በማመሳሰል የቱሪስት መነሃሪያ ይሆንብናል ከሚል ፍራቻ በተለይም መለኮሳት አባቶች አጥብቀው ሲከራከሩ ተስተውለዋል፡፡

በሌላ በኩል አይጠበቅ የሚል አላማ ባይኖራቸውም የጥበቃ አላማውን ሙሉ ለሙሉ ያልደገፉበት ሁኔታ መኖሩን ከዳልሸሃ፣ ሰቋርና አብረንታንት ገዳም አባቶች ተወክለው የመጡ መለኮሳት አባቶች ከሚያቀርቡት ሐሳብ ለመረዳት ተችሏል ::

በአጠቃላይ ከወረዳ አመራሮች እንዲሁም ከአጎራባች ቀበሌዎች የህብረተሰብ ተወካዮች ሲቀርብ የነበረው ሀሳብ የሚያበረታታና ለወደፊቱ ለሀብቱ መጠበቅ ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አመላካች ነው፡፡
ስለሆነም ለወደፊቱ የወረዳው አመራሮች ከአውደ ጥናቱ ቀጥሎ ባሉት ጊዜያት በቅንጅት ወደ ህብረተሰቡ በመግባትና የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ግንዛቤን በማህበረሰቡ ውስጥ በማስፋት ሀብቱ እንዲጠበቅ የበኩላቸውን እንደሚወጡና ቀሪ ስራዎች ተግባራዊ እንደሚሆኑ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

በውይይቱ መጨረሻም በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

1. አርማደጋ እንዲጠበቅ የመንግስት ውሳኔ ስለሆነ ወደፊት በጉዳዩ ላይ ህዝቡና የደጋሙ አባቶች ተወያይተውበት መቀበልና መስማማት እንዳለባቸው በቀጣይም ተመሳሳይ የምክክር መድረክ ተዘጋጅቶች በጥበቃው ላይ የመጨረሻ ስምምነት ላይ እንዲደረስ፣
2. አርማደጋ ሲጠበቅ በገዳሙ ህግና ስርዓት ሆኖ ከፓርክ ይልቅ የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራ እንደሚሆንና ከተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ በስተቀር ለቱሪዝም አገልግሎት እንደማይውል፣
3. የደኑ የጥበቃ ቤቶች የሚሰሩት በአዋሳኝ ቀበሌዎች ሀገር ቤት ውስጥ እንደሚሆን፣
4. የወል መሬቶቻቸውን ለእርሻ አውለው ከብቶቻቸውን በአርማደጋ ደን ውስጥ የሚያሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በህግ እንደሚጠየቁና ሊቀጡ እንደሚችሉ፣

5. በስራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች

በስራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና ቦታው ላይ በክለላ ኮሚቴው የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

5.1. ያጋጠሙ ችግሮች

1. በጨውበር ቀበሌ አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች ከተፈጥሮ ደኑ የሚያገኙትን የግል ጥቅም (ግጦሽ፣ ሽመል እና ደን ጭፍጨፋ) ለማስጠበቅ የአካባቢውን ህብረተሰብ በማስተባበርና በማሳመፅ የክለላ ስራው እንዳይካሄድ ማድረጋቸው፣
2. ቀደም ሲል የክለላው ስራ ከመካሄዱ በፊት የተፈጥሮ ደኑ እንደሚከለልና እንደሚጠበቅ፣ ስለክለላው ዓላማና ታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ወደፊት ስለሚኖረው አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ ሀገራዊና ዓለምቀፋዊ ጠቀሜታ እና ስነ ምህዳራዊ አስተዋፅዖ ወረዳው የተለያዩ መድረኮችን በመጠቀም በአጎራባች ቀበሌዎች ለሚኖረው ህብረተሰብ ሰፊ ግንዛቤ እንዲኖረውና ግልፅ እንዲሆን ባለማድረጉ ምክንያት የክለላ ኮሚቴ አባል የሆኑ የማህበረሰቡ ተወካዮችን ለማሳመን ረጅም ጊዜ መውሰዱ፤ ከስምምነት በኋላ አንዳንድ የክለላ ኮሚቴው አባላት ቃለ ጉባኤው ላይ ፊርማቸውን ለማስቀመጥ ፈቃደኛ አለመሆን፤ ለመፈረም ፈቃደኛ ያልሆኑ ግለሰቦችም የክለላውን

ዓላማ አዛብቶ ለህብረተሰቡ በመንገር ሰፊው ህዝብ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረጋቸው፣

3. የአዋሳኝ ቀበሌዎች የማህበረሰብ ተወካዮችን ስለክለላው ለማወያየትና ለማሳመን የቀበሌ አመራርና የኮሚቴ አባላት በተባለው ስዓት ተሟልተው አለመገኘት፣
4. ቦታው ባለው ውጣ ውረድ ምክንያት ለስራ ዓመች ባለመሆኑ የስራ መጓተት መከሰቱ፣
5. የወልድባ ገዳም አባቶች የተፈጥሮ ደኑ በጥብቅ ስፍራነት ተከልሎ እንዲጠበቅና ከጥበቃው ጋር ተያይዞ የመንግስትን እርዳታ አንፈልግም ማለታቸው፣

5.2. የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

1. በጨውበር ቀበሌ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት በመጀመሪያ ወደ 40 ከሚሆኑ የሀገር ሽማግሌና የኃይማኖት መሪ ከሆኑ የህበረተሰብ ክፍሎች ጋር በኋላም ወደ 180 ከሚሆኑ የቀበሌ ማህበረሰብ ጋር የወረዳው አመራሮች በተገኙበት ውጤታማ ሳይሆን ቢቀርም ችግሩን በውይይት ለመፍታት መሞከሩ፣
2. በጨውበር ቀበሌ ውስጥ በተፈጠረው ‹‹የአናስከልልም›› ሀሳብ ምክንያት በወቅቱ ክለላው ባልተካሄደባቸው የአዲአረጋይና በርማሪያም ቀበሌዎችም ተመሳሳይ ሁኔታ ይከስታል የሚል ስጋት በመፈጠሩ ተጨማሪ የሰው ሃይል በማስመደብ በሁለቱ ቀበሌዎች በኩል ያለው የተፈጥሮ ደኑ ክፍል እንዲከለል መደረጉ፣
3. ትርፍ ጊዜንና ከጥዋቱ 12 ስዓት እስከ ምሽቱ 12 ስዓት አንዳንዴም ሌሊት በጨረቃ እንዲሁም ቅዳሜና እሁድን ያለማቋረጥ በመስራት የባከኑ ጊዜያትን በማካካስ ስራን ማጠናቀቅ፣
4. ከክለላው በኋላ የክልል፣ የዞንና የወረዳ አመራርና ባለሙዎች፣ የቀበሌ አመራርና የህብረተሰብ ተወካዮች እንዲሁም የዋልድባ ገዳም አባቶች ተወካዮች በድምሩ ወደ 55 ሰዎች በተገኙበት በተፈጥሮ ደኑ ዙሪያ በተደረገው የምክክር አውደ ጥናት በተለይም ለህዝቡ ተወካዮችና ለገዳሙ አባቶች ስለክለላው ዓላማ የተሻለ ግንዛቤ እንዲይዙ ጥረት መደረጉ፣
5. የሰሜን ጎንደር ሀገረስብከት በተለይም አርማደጋ እንዲጠበቅ የገዳሙን አባቶች በማሳመን በኩል የሊቀ ጳጳሱ ሚና አስፈላጊ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ብፁዕነታቸው እገዛ እንዲያደርጉ መጀመሪያ በአካል በመቅረብ ስለችግሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና በኋላም ከእሳቸው በቀረበው ጥያቄ መሰረት የዝርዝር ጥናቱን የክለላውን ሪፖርት በማጠቃለል አጭር ማስተዋሻ ለመልክ ጥረት መደረጉ፣

6. ወደፊት መከናወን ያለባቸው ስራዎች

ከድንበር ክለላው በኋላ በትኩረት መሰራት ያለባቸው ስራዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ጨውበር ላይ የተፈጠረውን ችግር መፍታትና የክለላ ስራውን ማጠናቀቅ፣

- ► የተፈጥሮ ደኑ በዋነኛነት ከልቅ ግጦሽና ቅራት፣ የሰደድ እሳት፣ ደን ጭፍጨፋ እና ህገ ወጥ አደን ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰበት እና ሃብቱን እያጣነው ስለሆነ ጊዜ ሳይሰጠው በፍጥነት የክላላ ስራው እንዲጠናቀቅ ማድረግ፣

❖ ሕጋዊ እውቅና ማሰጠት፣
- ► በተለያዩ ጥናቶች የተገኙትን ማጠቃለያዎች መነሻ በማድረግ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ጠቀሜታዎች ለተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ያላቸውን አስተዋፅዖ በማረጋገጥ የታሳቢ ጥብቅ ስፍራው ዳር ደንበር በህግ እንዲወሰን ደጋፊ ሰነድና ረቂቅ አዋጅ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ለውሣኔ ማቅረብና ሕጋዊ ሰውነት ማሰጠት፣

❖ የልማትና ጥበቃውን ስራ መስራት፣
- ► የመዋቅር ዝግጅት፣ የሰራተኛ ቀጥር፣ ጽ/ቤት መክፈት፣
- ► የልማትና ጥበቃ ስራውን ተረክቦ ማስቀጠል፣
- ► ከጽ/ቤት ግንባታ ጀምሮ ለጥበቃና ልማት አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ ልማትና የግንባታ ቦታዎችን በጥናት መለየትና አስፈላጊውን ግብዓት ለማሟላት የገንዘብ ድጋፍ ማፈላለግ

❖ በአርማዳጋ የተፈጥሮ ደን ልማትና ጥበቃ ላይ የአጋር አካላትን ተሳትፎ፣ ተግባራትና ኃላፊነቶችን መለየትና ማሳወቅ፣
❖ በየቀበሌው ኮንፈረንስ በማካሄድ በአርማዳጋ የተፈጥሮ ደን ጥበቃ ላይ ህብረተሰቡን የማሳመን ስራ መስራት፣
❖ የተፈጥሮ ደኑ በሁለት ክልሎች መካከል ላይ የሚገኝ በመሆኑ ወደፊት ፌደራል በጉዳዩ ላይ ተሳትፎ የሚያደርግበትን ሁኔታ ማፈላለግ፣

7. የአጋር አካላትን ተሳትፎ፣ ተግባራትና ኃላፊነቶች

በተለያዩ የጥናት፣ የክለላና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች የሚመለከታቸውን አጋር አካላት ማሣተፍ፣ ማሳወቅና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡና ዘላቂ አጋርነታቸውን ለማረጋገጥ፣ ወቅታዊ ግንኙነትና ተግባራዊ እንቅስቀሴ ማድረግ፣

7.1. የክልል፣ ዞንና ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ሴክተር

❖ ከሀገረ ስብከት፣ ቤተክህነት እና ከሚመለከታቸው የገዳሙ መሪዎች ጋር በመሆን በደኑ አጠባበቅ ስርዓት ላይ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ፣
❖ ከቀበሌ አመራር አካላት ጋር በመሆን ለአካባቢው ማህበረሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት (ዞንና ወረዳ)፣
❖ ከክለላ ስራ በኋላ የተፈጥሮ ደኑ በአዋጅ ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ ማስቻል (ክልል)፣
❖ የመዋቅር ዝግጅት፣ የሰራተኛ ቀጥር፣ ጽ/ቤት መክፈት፣
❖ የልማትና ጥበቃ ስራውን ተረክቦ ማስቀጠል፣
❖ ለጥበቃና ልማት አስፈላጊ የሆኑ የመሠረተ ልማትና የግንባታ ቦታዎችን በጥናት መለየትና አስፈላጊውን ግብዓት ማፈላለግ፣
❖ ከፌደራል ጋር በደኑ ጥበቃ ላይ ግንኙነት መፍጠርና መምከር፣
❖ በጨውበር የተፈጠረው ችግር ሲፈታ የቀረውን የክለላ ስራ ማጠናቀቅ፣

7.2. የክልል፣ ዞንና ወረዳ መስተዳደር ሴክተር

- በተፈጥሮ ደኑ የጥበቃ ስርዓት የሚነሱ ማንኛውንም አሉታዊ አመለካከቶችን ለማስወገድ የቀበሌ አመራሮችንና ማህበረሰቡን የማሳመን ስራ መስራት (ዞንና ወረዳ)፣
- ቦታው በአዋጅ ህጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ እገዛ ማድረግ (ክልል)፣
- በአዋጅ እስኪቋቋም ድረስ በየቀበሌው የተቋቋሙ የደን ግብረ ኃይሎችንና ሚሊሻዎችን በመጠቀም የተጠናከረ ጥበቃ ማካሄድ (ዞንና ወረዳ)፣
- ከደኑ ጥበቃ ጋር ተያይዞ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች እንዲካሄዱ ማስተባበር (ዞንና ወረዳ)፣
- በአጎራባች ቀበሌዎች በፊት የነበረው የመሬት ስሪት በተለይም የግጦሽ ቦታዎች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ማስተባበር/ማመቻቸት (ዞንና ወረዳ)፣
- በጨውበር ቀበሌ ከክለላውጋር ተያይዞ የተፈጠረው ችግር እንዲፈታ ማድረግ እና ወደ ሌሎች አዋሳኝ ወደ ሆኑ ቀበሌዎች እንዳይዛመት ማድረግ (ዞንና ወረዳ)፣

7.3. ክልል፣ ዞንና ወረዳ ግብርና ሴክተር

- በአጎራባች ቀበሌዎች አካባቢ የሚገኙ የቤት እንስሳት ዝርያዎችን በማሻሻል ቁጥራቸውን መቀነስ እና ዘመናዊ የቤት እንስሳት እርባታ ዘዴዎችን ማስፋፋት፣
- በየቀበሌዎች የተቋቋሙ የደን ግብረ ኃይሎችን ማጠናከርና ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ፣
- ከሰሜን ጎንደር ዞን የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና አጠቃቀም ፕሮግራም የተመደበውን በጀት በመጠቀም የአካባቢ ሚሊሻዎችን በጊዜያዊነት መቅጠርና የተጠናከረ ጥበቃ ማካሄድ፣
- በአጎራባች ቀበሌዎች የደን ልማት ስራ በስፋት ማካሄድ፣
- በአጎራባች ቀበሌዎች የእርሻና የግጦሽ መሬቶችን ምርታማነት ማሳደግ፣
- ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር በመሆን የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት፣
- የዕጣን ዛፍ በምርት ብዛት ምክንያት የተጎዳ ስለሆነ እስኪያገግም ድረስ ማረፍ እንዲችል በዚህ ዙሪያ የወጣው መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ፣
- በየቀበሌው የዕጣን ዛፍና ሽመል ልማት ማካሄድ፣
- በወንዞች አካባቢ በዓሳና በሌሎች ሃብቶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመከላከል የፀረ-አረምና ተባይ መድኃኒቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋላቸውን በባለሙያ አማካኝነት ማረጋገጥ፣

7.4. ክልል፣ ዞንና ወረዳ አካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሴክተር

- በአጎራባች ቀበሌዎች በፊት የነበረው የመሬት ስሪት በተለይም የግጦሽ ቦታዎች ወደ ነበሩበት መመለስ፣
- የአካባቢው የተፈጥሮ ሃብት እንዲጠበቅ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት፣
- በት/ቤቶች የአካባቢ እንክብካቤ ክበባት እንዲስፋፉ፣ እንዲጠናከሩና ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ፣
- የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ማካሄድ፣

7.5. ክልል፣ ዞንና ወረዳ አስተዳደር ፀጥታ ሴክተር

- በክለላ ስራው ወቅት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፣
- በተፈጥሮ ደኑና በአካባቢው የሚፈፀሙ ህገውጥ የተፈጥሮ ሃብት ውድመት መከላከልና መቆጣጠር፣
- ለግጦሽ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ እንስሳትን መከላከል፣

7.6. ክልል፣ ዞንና ወረዳ ፍትህ ሴክተር

- በአጎራባች ቀበሌዎች ለሚገኘው ማህበረሰብ የንቃተ ህግ ትምህርት መስጠት፣
- በተፈጥሮ ደኑና አካባቢው በሚገኘው የተፈጥሮ ሃብት ላይ ህገ ወጥ ድርጊት (አደን፣ መርዝ መጠቀም፣ ልቅ ግጦሽ፣ የሰደድ እሳት) የሚፈፅሙ ግለሰቦች ፈጣንና አስተማሪ የሆነ ውሳኔ ማሰጠት፣

7.7. ክልል፣ ዞንና ወረዳ ጤና ሴክተር

- ያልተፈለጉ መድኃኒት በሚያቀርቡ የመድኃኒት መደበሮችና ሱቆች ላይ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ፣
  - ► ለምስሌ ዓሳ ለማስገር በእንስያ፣ ዛሪማ፣ ድቅቆ እና እንዞ ወንዞች ላይ መርዝ መጠቀም፣

7.8. የሰሜን ጎንደር ዞን የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና አጠቃቀም ፕሮግራም

- አስፈላጊውን በጀት በመመደብ ለክለላውና ለጥበቃ ስራው እገዛ ማድረግ፣
- ከክለላው በኋላ በጥብቅ ስፍራው ውስጥ ለሚካሄደው የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ስራ እገዛ ማድረግ፣

8. ዕዝል

8.1. የፀደቀ የቀበሌ የክለላ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ

ቀን....15/04/04.....

በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን በአዲአርቃይ ወረዳ በ.....ኦ.ሊ.....ቀበሌ የአርማደጋ የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ እና የቀበሌውን ወሰን ክለላ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ፣

የክለላው መነሻ ቦታ..የዱቅቅና ዘለማ መዳጣመር
የክለላ ስራው የተጀመረበት ቀን...13/04/04....
ክለላው የተጀመረበት ሰዓት...12:00.....
የስብሰባው ቦታ.....ዱብሸሃ.....
የስብሰባው ቀን.....15/04/04.....
የስብሰባው ሰዓት...10:30.....

	ተሳታፊዎች	የስራ ድርሻ
1.	አቶ መስፍን አስናቀው	የወረዳው አስ/ፊናንስ ፋ/ሥራ ኃላፊ
2.	ኃይሉ አስፋ ቅስቀስ	የአዲአርቃይ ወረዳ ፓሊስ አዛዥ
3.	አቶ ጎጋ ዋናው	የአዲ ቀበሌ ቋሚ አስተዳዳሪ
4.	አቶ ብልስቲ ፈጠነ	የ ግ/ት /ፓርቲ ሊቀ ግለመንበር
5.	አቶ ይሐንስ መሳይው	የ ግ/ት /ፓርቲ ሊቀ' ግለመንበር
6.	አቶ ዕጠታው አዓመ	የአዲአርቃይ ወረዳ ፍካሳ/ፋ/መ/አስ/አመታቃቃ ሠራተኛ
7.	አቶ መሳይው ባዬ	የአዲ ቀበሌ ፖለቲከር ስብሳቢ
8.	አቶ ገብሄው ወ/ገብርኤል	የሃገር ሽማግሌ
9.	አቶ አደጉው ሊተወለ	የሃገር ሽማግሌ
10.	ወ/ሮ አበባ አለቃሃ	የቀበሌው የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ
11.	አቶ ሰዘአግና ዳኖሬ	ረዳት መምህር
12.	አቶ ገዳው ተፈራ	የሃገር ሽማግሌ
13.	አቶ ጥላሁ ፀጋው	ቀበለቀዋና አፈ ጉባኤ
14.	አቶ ሙሳው አደጉው	የቀበሌው ሀዋስ ሊ ቀመንጠር
15.	አቶ ታዲስ አብይ	የቀበሌው የእንስሳት ጠና ባለሙያ
16.	አቶ አባገው ተዘራ	የቀበሌው ዐዲሰ
17.	አቶ ሰናማው ወሰኸኘሃ	የቀበሌው ፀሐፊ
18.	ወ/ሮ ሌዛዊኝ መንገስ	የቀበሌው ጤና ኤክስቴንሽን ተመ

አለንበት።

አጀንዳ፡

በ.....ኦ.ሊ.....ቀበሌ አስተዳደር በኩል የአርማደጋ የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ ወሰን ለመከለልና ለማፅደቅ፣

በታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ ውስጥ የሚገኙትን የብዝሃ ህይወት ሃብቶች ለመጠበቅ፣ ጤናማ ስርዓተ ምህዳር ለመፍጠር፣ ዘለቂታ ባለው መንገድ ለመንከባከብ፣ ኩቱሪዝም ሊገኝ ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ

ጠቅመኛሩ የአህ ኣጀል ኣመፋጠፀ ኣኳያ ታካቢ ፓርኩ ያለው ኣፈተቀፅኦ ኣፍተኛ መሆኑን ኣብን ቢው ኣፋይዶ ማጠሪቦን: ለመሸጣት ኣገለግሎት: ቦታን: ተጠጠማሪ: ኣፈተያየት ተሳታፊ ውይይት ተካሂዱ: ፓርኩ መከለለ ኣንዲለበት ለመተጣጠን: የሚከለለው: ውሳኔ ሰጭ ኣካላት ኣፈተለሳፈል::

1. የታካቢ: ኣባት ዒት: ወሰን: ኣቀባበው: ለኣተፀመቱ ኣጭ ጣጣ: ኣዳጋቹ: ዘሀመ: መተኛ ጠመሩን ሳመሳኩት ወዲ: ዒሳለ: ኣጭጣጭ: የዘሀማን: ወዳዝ: ወዲ ወሰን: ለመጀሪያ: ኮንፈብ: 1 ኣመስ 1ፋፀ ጀሀስ: የጀፔኤስ ጓሳኖን: ለመው ኣጀሩ ለሰ ጣያዊ: ቀለጭ: ኣለፉን ለጣጀሪያ: ክለንው: ያኳኳጅን ሰሀዶ: ኮንፀ: የተለ ፊት: ኮጨሰን: የቀባበው ዩያኑ: ወሰኔ! ኣለከቻት: መሆኑው: ገለተለያየ ጀጣፀ: ወሰፍ::

2. የሀቃለ ንባቹ: ኣተወሰዱት: የጀፔኤስ ኦ: ኮርዲኔቻት: ጋር: ተጀዞ: ለኣዲኣርቃይ ወሀዶ: ኣኣተዳጀር: ለኣካቢ ኣበቃ: ለቀባበው: ኣኣተዳደርና ለ ሊሮው: ለቀባበው: ማሀተጭ: ተሠጠጦ: ኣሩጀ ኣንጅ: ኦቲ: ኦሩጀደርኣና: ኣሩጀዲዶጅ: ገለተለያየ: ጀጣፀ: ተኣጣመተን: ለ15/04/ዐዛ ኣ ቀ ን: 11:00 ኣኣን የጀጨበ: ክለንውና: የሀፓን ኦፀ: ኣጠቃለናል::

ተ.ቁ	የወርሀች ኣብይ ኣዐዲ ኣጣዐ	ፊርማ
1	አቶ መሐመድ አህመድ	
2	ኃይ3 አለቃ ቅዳሜአለ	
3	አቶ ካጋ ቀኘው	
4	አቶ ለገሰ ሬጌጎ	
5	አቶ የሕንጎስ ወሰነ	
6	አቶ ኃጎተሙ ዲኒቂጦ	
7	አቶ ወሰነ	
8	ገለጸለ መ/ገጦርኤል	
9	አቶ አጸፈለ ለተመለጎ	
10	መ/ሮ አለባ አጦሮሀ	
11	ዐዐ ወሪ ደርሀር	
12	ገቢው ለተመሰጎ ተሰ	ገቢሪዘ-ተሳ ፍ
13	ዐገለ መዐዐ	
14	አቶ አጸፈለ	
15	አቶ ታከለ አለቀ	
16	አቶ ኦጎገመ ተዘሩ	
17	መ/ሮ ለዘቂች መንገሻ	
18	አቶ መርዖዲመ መርቻ ጎዳ	

ቀን 21/4/ዋ

በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን በአዲአርቃይ ወረዳ በ...ጎጠራ ፋርጃ.....ቀበሌ የአርማደጋ የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ እና የቀበሌውን ወሰን ክለላ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ፣

የክለላው መነሻ ቦታ....ሳመ ኦጋ ርዕ እንርስቲያን
የክለላ ስራው የተጀመረበት ቀን...19/04/04...
ክለላው የተጀመረበት ሰዓት.....3:00.....
የስብሰባው ቦታ.....ፋርጃ.....
የስብሰባው ቀን....21/04/04.....
የስብሰባው ሰዓት.....5:00.....

ተሳታፊዎች

1. ኒች መስተንግዶ አለሚቀው
2. ኒች ማንይፍዮ አለሳያለማው
3. ኒች ወሃሩ ችረሁን
4. ኒች ገ/መስቀል የኃረገኝ
5. ወገች ልክንሽ ጌሩነህ
6. ኒች አለሰ ተሸመ
7. ኑ ቄስ ንጋቴ ገጠሮ
8. ኒኅ ገ/ማርያም ወ/ጊዮርጊስ
9. ኒኅ ቄስ ምህንዳሩ አደሀ
10. ኒች ፍገጌ መሰመ
11. ኒች ፀጋው መሰሃን
12. ኒች ኒአማለዩ መሰሪያ
13. መሪ ኒትምነሩ ታምሪች
14. ሰሪ ሰለደነሽ ችንሰሰ
15. ኒች ሳመይነህ ኪሳ
16. ኒች ዮሃንስ መሰሪያ
17. ኒች ሰመስቲ ፍሠነ
18. ኒች ሃ ሠገው ሳዓነሮ

የስራ ድርሻ

የኢጽ-ዓ ርቃደ ወረዳ ኒአተጽዱር ፀኛታ ቃለመጅ ሃገ
የአከ.ኢርቃደ ርዕሳ መ/ወ/ል ቅ/ርሔች ሃገሰ
የንጠሩ ፋጅም ቃለርህ አለተዲዛሁ
የንጠሩ ፋጅም ቃለርህ ሳመ/ አለተዲዛሪ
የንጠሩ ፋጅም ቃለርህ አገሽ/መ/አገል ሰለምያ
የቃለርህው የመሰች ኑሮሜቴ ሀጠሳሪ
የ ሃ ይ ወ ዲ ች መ ሪ
የ ሃ ጅር ኢ/መሠሪች ገጻናው ተመኒይ
የ ሃ ይ ወ ዲ ች ር ሪ
የ ሀ ገ ር ቅ ማ ግ ር ህ
የቃለርህው ደ/ሩ አለ ኢ ያ ጅ
የቃለርህው የ ታ ሪ ፃ ዩ ሠ ነ ሰለምያ
ር ዕ ሳ መ ም ህ ር
የቃለርህው ጅ ቃ ል ጉ ጻ ሬ
የ ሳ ን ት ቃለርህ አለተዲዛሁ
የ ሳ ህ ሠ ፣ ት ሬ ሠ ነ ኦ ፣ ፓ ል/መ/ሊ ዩ ሰለምያ
የ ገ ዛ ሀ ፣ ት ሬ ሠ ነ ኦ ፣ ፓ ል/ሊ ዩ ሰለምያ
የኢጽ ኢርቃደ ወረዳ ኒአገ/መ/አ/አ ይ ል ሬ ታ ሰለም

አለንበት።

አጀንዳ፡

በ...ጎጠራ ፋርጃ.....ቀበሌ አስተዳደር በኩል የአርማደጋ የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ ወሰን ለመከለልና ለማፅደቅ፣

በታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ ውስጥ የሚገኙትን የብዝሃ ህይወት ሃብቶች ለመጠበቅ፣ ጤናማ ስርዓተ ምህዳር ለመፍጠር፣ ዘለቂታ ባለው መንገድ ለመንከባከብ፣ ከቱሪዝም ሊገኝ ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ

ጠቀሜታና የስራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ ታሳቢ ፓርኩ ያለው አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑን ሰብሳቢው ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት ከገለጹ በኋላ በተሰብሳቢዎች ተጨማሪ አስተያየት ተሰጥቶና ውይይት ተካሂዶ ፓርኩ መከለል እንዳለበት በመተማመን የወሰን ከላይ ኮሚቴው ያለምንም ልዩነት የሚከተለውን የውሳኔ ሃሳብ አስተላልፏል፡፡

የውሳኔ ሐሳብ

1. የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን ወሰን ከቀበሌው ሰገሞን ጣቢያ አቀጣጫ ከአገ ጎመኤለ ሰፈ ፈርሸጌ በመነሳት ሰንተሰብሰብንበት ጣቢያ ሸንጎ፡ ጣዉሰን መለያ ቀጥር 1፱፭ ሰመነጥን አስከንጀን የውሰን መለያ ቀጥር ፫ ሲሆን ከመጨው ሰርና ካብሮ ዓድታ ቀጠሌ ቻን ዉሰጥ ወይመ ሳዲሳንን፡ የቪሊኤስ ንብረትን ሰመውሰድና የጎጣየዉ ተሳጥ፡ ገመሰን ሰመሄጠ፡ አነሰሳ ያሳሳሄደ፡ ሰሀዩን፡ ሳሰዩ የሰጠቀሱን ቁጥጥር ሲኖር የቀጠሉ፡ ወሰን፡ ጠበቆበዉ፡ ያለ ጣጠፋ ሰደናን፡ የወሰደ፡ ጠሠኝ አዘሀ ወሰን፡ ለተቀመጠው ፅ.ር ሰንሩ እናዉጋወግሏል፡፡

2. ይህ የቀበሌው የፓርክ ወሰን ክለላ ቃለ ጉባኤ ከተወሰዱት የጅፒኤስ ኮርዲኔቶች ጋር ተያይዞ ለአዲአርቃይ ወረዳ አስተዳደር፣ ለአካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት፣ ለቀበሌው አስተዳደርና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ በቀበሌው ማህተም ተረጋግጦ አንዳንድ ኮፒ እንዲደርስና እንዲጸድቅ ባልተለያየ ድምጽ ተስማምተን በ 21/04/04 ቀን ከቀኑ በ 6:00 ሰዓት የድንበር ክለላውንና የሪፖርት ስራ አጠቃለናል፡፡

የኮሚቴው አባላት ስም	ፊርማ
1. አቶ መሀመድ አህመቀው	
2. አቶ ወንዱፍሮ አሰማው	
3. አቶ ወሃሌ ጀብሀን	
4. አቶ ገ/መስቀል ይሳቅ	
5. ወ/ሪ ሸክገሽ ጀሩሀህ	
6. አቶ አለሌ ተሾመ	
7. ቄስ ንጋቱ ገጠሌ	
8. አብ ገ/ማሪያም ወ/ጻዲቅ	
9. አብ ቄስ ጥመጋናው አደመ	
10. አቶ ሞጎስ መሰመ	
11. አቶ ሸጋው መሀንን	
12. አቶ አለማሃሌ መሰሀፃ	
13. መ/ር አትፃንሩ ታፃሌን	
14. ወ/ሮ ለሊዩንሽ አንለል ሌ	
15. አቶ ለማጌህ ካሳ	
16. አቶ ዩኃንስ መሰሀፃ	
17. አቶ ለልአt ፍጠነ	
18. አቶ ሻጠለሀ ዓዲም	

ቀን...2/05/04.....

በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን በአዲአርቃይ ወረዳ በ..አዲአሁጋይ.....ቀበሌ የአርማደጋ የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ እና የቀበሌውን ወሰን ክለላ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ፣

የክለላው መነሻ ቦታ....አዲሀውልወልገ /ማይጀቆገ
የክለላ ስራው የተጀመረበት ቀን...2/05/04.....
ክለላው የተጀመረበት ሰዓት...12:00.....
የስብሰባው ቦታ.....ማይማውሲ /ግሀደማሪ.....
የስብሰባው ቀን.....2/05/04.....
የስብሰባው ሰዓት.....5:00.....

ተሳታፊዎች	የስራ ድርሻ
1. ኃይሉ አዛናው ሮሊኤ	የቀለቀው ቁና አለተኳንቤ
2. አንቶ መርሻ ታደሰ	የቀለቀው አለተኳንሬ ልጃታ
3. አንተ መርሀዬ ግሽጌዳዬር	የቀለቀው አለ/ኛ/ወላአ/ኢ ባለማዕረ
4. አቶ መስተዳድር አጥናፍ	የቀለቀው የተሰማ ሀጎት ባለማዕረ
5. አንተ መለሳለሙ ታዲሰ	የቀለቀው የግጠርና ሴቲርቫዳዘር
6. አንተ አለፋው መሙሸ	የሀገር ሽማግሌ
7. አንተ አለሰ ብጅሮ	የሀገር ሽማግሌ
8. አንተ አስማ ሽጎ ጋዝሽጎ	የሀገር ሽማግሌ
9. አንተ አለማሬ ለለሂ	የቀለቀው ኑማንቤዳ
10. አንተ ንጉሱ አገተ	የቀለቀው መሪሁ
11. አንተ አዲሱ ገ/ቂሀዲ	የቀለቀው መሪሁ
12. አቶ መሙሩቴታ አለሳቀው	የወረዳው ገለ/ፀሃፊ ልለቤት ቴሪሲ
13. አቶ ሳይን አለፋ ቅለቀለ	የወረዳው ፓሊስ/አለተኳንሬ ታዲሂ/
14. አንተ ለመለተ ፈጠነ	የግ/ት/ለዩ ባለመጽ
15. አንተ ዶ/ር አመሀዬ	የግ/ት/ለዩ ባለመጽ
16. አንተ ኃ.ተ.መ ዓ.ም	የወረዳው አለ/ኛ/ወላአ/ኢ ልለቤት ለለ
17. አንተ መሙሩቀን አለለመ	የቀለቀው ወጣቶች ለ/ህለሬ/ወንሬ
18.....	.....

አለንበት።

አጀንዳ፡

በ.....አዲአሁጋይ.....ቀበሌ አስተዳደር በኩል የአርማደጋ የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ ወሰን ለመከለልና ለማፅደቅ፣

በታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ ውስጥ የሚገኙትን የብዝሃ ህይወት ሃብቶች ለመጠበቅ፣ ጤናማ ስርዓተ ምህዳር ለመፍጠር፣ ዘለቄታ ባለው መንገድ ለመንከባከብ፣ ከቱሪዝም ሊገኝ ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ

ጠቀሜታና የስራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ ታሳቢ ፓርኩ ያለው አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑን ሰብሳቢው ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት ከገለጹ በኋላ በተሰብሳቢዎች ተጨማሪ አስተያየት ተሰጥቶና ውይይት ተካሂዶ ፓርኩ መከለል እንዳለበት በመተማመን የወሰን ከላይ ኮሚቴው ያለምንም ልዩነት የሚከተለውን የውሳኔ ሃሳብ አስተላልፏል፡፡

የውሳኔ ሐሳብ

1. የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን ወሰን ከቀበሌው ሳሚያን ጭኢሆስ አቅጣጫ ፊቶ ሸለው ማይቆላ አተላለው ቦታ በመነሳት ወዲ ዱለብ ሳትጣጫ ሳላውሃን መደያ ቁንፍሳ ንጀሳ ጅአሳ ሳዐሳ የእንሰሳያና የእንዘ ወንዙን መገናኛ ቦታ (መዳማዕዐን) ዱሩስ ወንዙን ወዲ ወሰን ለማዲለማ የጂ ፒ ኤስ ኮኦዲኔትን ለመያዝ የሰማ ያቆ ቀለሎ ክልሎች ለማዲለማ እለነላውን ያካላይን ሲሆን ከላይ የተጠቀሰች ቀናሽን የቀበሌውና የያን ክልሉ ወሰን መሆናቸውን ገልጽለያየ ዱካለች ወሰነን አዘዢ ቦታ ሁኖማችንን ለማስቀመጥ ችሏልጠናል፡

2. ይህ የቀበሌው የፓርክ ወሰን ክለላ ቃለ ጉባኤ ከተወሰዱት የጅፒኤስ ኮርዲኔቶች ጋር ተያይዞ ለአዲአርቃይ ወረዳ አስተዳደር፣ ለአካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት፣ ለቀበሌው አስተዳደርና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ በቀበሌው ማህተም ተረጋግጦ አንዳንድ ኮፒ እንዲደርስና እንዲጸድቅ ባልተለያየ ድምጽ ተስማምተን በ 2/05/04 ቀን ከቀኑ በ 5 ስዓት የድንበር ክለላውንና የሪፖርት ስራ አጠቃለናል፡፡

የኮሚቴው አባላት ስም		ፊርማ
1 አቶ አዘናጋው ፈረዳ		
2 አቶ መርሻ ታደሰ		
3 አቶ ጠርማይ ቀኝ ለይዲር		
4 አቶ መስተፋ አለሙሳ		
5 አቶ መለሳው ታዲሳ		
6 አቶ አለፋው መሙሙ	ሃ	
7 አቶ አለለ ለይሁ		ሃበበ ስንፋሬ
8 አቶ አለማየሽ ገዛኸኝ		
9 አቶ አለሳዲር ለለዲ		
10 አቶ ንጉሴ ሸገተ		
11 አቶ አሳሉ ገቀሃዲ		
12 አቶ መሰለ ቦታ አለሳ ቀሙ		
13 አቶ ሳይን አለፋ ቅንቀሳ		
14 አቶ ለለለቴ ፎጣን		
15 አቶ ዩ ኤንን መሰለ ዐ		
16 አቶ ኤክታለው ሳሳላዉ		
17 አቶ መሰለቱን አለለው		
18		

ቀን..03/05/04.....

በስሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን በአዲአርቃይ ወረዳ በ...ብደማይያጫ....ቀበሌ የአርማዳጋ የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ እና የቀበሌውን ወሰን ክለላ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ፣

የክለላው መነሻ ቦታ.....መደለማጭርሳ/ጭዳማር..
የክለላ ስራው የተጀመረበት ቀን...03/05/04.....
ክለላው የተጀመረበት ሰዓት...7:30.....
የስብሰባው ቦታ...የብደማይጫ የመንግስት ቀጠናዊ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት (መደለማጭርሳ)
የስብሰባው ቀን...03/05/04.....
የስብሰባው ሰዓት...11:30.....

ተሳታፊዎች	የስራ ድርሻ
1. አቶ መስፍን አለሳቀው	የወረዳው አስ/ፅ/ቤት ቋሚ ኮሚቴ
2. አቶ ፀጋሁን መሩ	የቦ.ር.መ.ሪ.ጽ.ቤ ቀ.ሰ.ሜ ዋና አስተዳዳሪ
3. መ/ር አዱ ገ/ጊዮርጊስ	ርዕሰ መምህር
4. መ/ት አትክልት ካጋ	የቀ.ሰ.ሜ ጽ.ሥ.አ.ፃ.ት
5. ኮ/ል ሲሳይ ሻ/ሀገን	የቀ.ሰ.ሜ ኮ/ፓ/አ.ሃ
6. አቶ ሽጋጥ ሰ.ሰ.ማ	የቀ.ሰ.ሜ አ.ኢ/ኦ/መ/አ/አ/ሰ.ሰ.ማ.ኃ
7. አቶ ኮ/ዘሪሁ መ.ሰ.ሰ.ው	የቀ.ሰ.ሜ ማ.ረ.ሻ ደ.ሀ.ን.ኦ.ር ፅ.ጥ.ኃ
8. አቶ ሰለሞ አ.ዲ.ስ	የቀ.ሰ.ሜ የ/ቤ/ቁ.ጥ.ር ጽ.ቤ ሰ.ሰ.ማ
9. አቶ ይ.ኔ.ን መ.ሀ.ሌ	የቀ.ሰ.ሜ ኑ/ስ/ሀ.ብ/ አ.ኗ.ሁ.ኔ ሰ.ሰ.ማ
10. አቶ አ.ለ.ባ.ው መ.ኮ.ኑ.ን	የቀ.ሰ.ሜ የ.ሕ.ክ.ል ሰ.ላ.ት ሰ.ሰ.ማ.ኃ
11. አቶ መ.ሰ.ፈ ሰ.ሰ.ይ.ነ.ህ	የቀ.ሰ.ሜ መ.ሰ.ፈ/ሰ/መ.ንጽ.ር
12. አቶ ተስፋሁን ዋ.ት.ኑ	የቀ.ሰ.ሜ ማ.ረ.ሻ
13. አቶ መ.ኘ.ን.ት ተ.ሃ.ፐ	የቀ.ሰ.ሜ አ.ፈ-ጉ.ባ.ኤ
14. አቶ ፀ.ሀ.ፐ አ.ስ.ቴ	የቀ.ሰ.ሜ መ.ሕ.ም.ሩ.ቴ.ኒ.ሄ
15. አቶ አ.ለ.ሌ ታ.ደ.ሰ	የቀ.ሰ.ሜ የ.ሠ.ር ስ.ማ.ኅ.ሰ.ሳ
16. አቶ ሻ/ሁን መ.ኘ.ን.ት	የቀ.ሰ.ሜ ማ.ረ.ሻ ደ.ሀ.ን.ኦ.ር ፀ.ሀ.ኤ
17. ጎ.ይ.ን አ.ሰ.ፋ ቅ.ል.ጭ.ስ	የወ.ረ.ዳ.ው ጋ.ሰ.ን አ.ስ.ተ.ዳ.ዳ.ር ተ.ወ.ካ.ይ
18. አቶ ጸ.ጎ.ን.ሳ መ.ኮ.ሀ.ፃ.ው	የ.ባ/ኑ/ፓ/ሰ/ ሰ.ላ.ም ሰ.ሰ.ማ.ኃ
19- አቶ ሰለሞ ፈጠነ	የ.ባ/ኑ /ፓ/ሰ/ ሰ.ላ.ም ሰ.ሰ.ማ.ኃ
አለንበት፡፡ 20- አቶ ኃ.ጎ.ተ.ሙ ዓ.ዓ.ም	የወ.ረ.ዳ.ው አ.ስ/ተ/መ/አ/አ/ፅ/ቤ.ት ሰ.ሰ.ማ.ኃ

አጀንዳ፡

በ.....በ.ደ.ማ.ያ.ጫ.....ቀበሌ አስተዳደር በኩል የአርማዳጋ የተፈጥሮ ደን ታሳቢ ብሔራዊ ፓርክ ወሰን ለመከለልና ለማፅደቅ፣

በታሳቢ ብሔራዊ ፓርኩ ውስጥ የሚገኙትን የብዝሃ ህይወት ሃብቶች ለመጠበቅ፣ ሴፍቲ ስርዓተ ምህዳር ለመፍጠር፣ ዘለቄታ ባለው መንገድ ለመንከባከብ፣ ከቱሪዝም ሊገኝ ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ

ጠቀሜታና የስራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ ታሳቢ ፓርኩ ያለው አስተዋፅዖ ከፍተኛ መሆኑን ሰብሳቢው ሰፋ ያለ ማብራሪያ በመስጠት ከገለጹ በኋላ በተሰብሳቢዎች ተጨማሪ አስተያየት ተሰጥቶና ውይይት ተካሂዶ ፓርኩ መከለል እንዳለበት በመተማመን የወሰን ከላይ ኮሚቴው ያለምንም ልዩነት የሚከተለውን የውሳኔ ሃሳብ አስተላልፏል፡፡

የውሳኔ ሐሳብ

1. የታሳቢ ብሄራዊ ፓርኩን ወሰን ከቀበሌው ለአተሞኽሀብ አቅጣጫ ወዲማሞወሽ (የጀንአደሩ እንሥ) መገናኛ ላይ በመነሳት ወዲዳሪብ አቅጣጫ፡ ከወሰን፡ መሃል፡ ቅኝ ሬ ሃወሃ ለመነሳት ላይ 468 የወሰን መለያ (የመጀመሪያ ባቲማርያም ቀበሌያችን ድንበር) ሽፋሌ የጂፒኤስ ንባብ ወንዙን፡ ተከትሎ፡ በመወሰደ፡ የስማያዊ፡ ቀላል፡ ምስክር በማክበሪያ፡ ክለላው፡ ያካሄዱን፡ ሊሠን፡ ሃላይ፡ የተጠቀሱት ቅኝሮች የቀበሌው የአርማሷ ዳን፡ ወሰን፡ መሠረትወን፡ ገጸተለያየ፡ ድምፅ፡ ማውሰኑንን፡ አዘኒ፡ ቦታን፡ ባተቀመጠው፡ ፊደሻን ኢናሬጋ ማጣሪ ፡!

2. ይህ የቀበሌው የፓርክ ወሰን ክለላ ቃለ ጉባኤ ከተወሰዱት የጅፒኤስ ኮርዲኔቶች ጋር ተያይዞ ለአዲአርቃይ ወረዳ አስተዳደር፣ ለአካባቢ ጥበቃ፣ መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ጽ/ቤት፣ ለቀበሌው አስተዳደርና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ በቀበሌው ማህተም ተረጋግጦ አንዳንድ ኮፒ እንዲደርስና እንዲጸድቅ ባልተለያየ ድምጽ ተስማምተን በ 2/05/04 ቀን ከቀኑ በ 12:00 ሰዓት የድንበር ክለላውንና የሪፖርት ስራ አጠቃለናል፡፡

የኮሚቴው አባላት ስም	ፊርማ
1. አቶ መሪጌታ አለሳቀው	
2. አቶ ጌታሁን መሩ	
3. መሪ አዲ ገ/ዮሐንስ	
4. ወ/ት አትክልወሽ ጎጋ	
5. ዮ/ወ ሊኦለ ኽሳሁን	
6. አቶ ጎጋሪ ሊሰመ	
7. አቶ ዘነለ መሰፈው	
8. አቶ ለማ አዴሉ	
9. አቶ ደጀን ማሀሌ	
10. አቶ አለባቸው መርሀን	
11. አቶ መሰፈቴ ለለይነህ	
12. አቶ ተስፋሁን ዋወሽ	
13. አቶ መኡንን ተስፋዩ	
14. አቶ ፀሀዩ አሰፋ	
15. አቶ አለሉ ተኢለ	
16. አቶ ኽሳሁን መኡንን	
17. ጎደን አለፋ ቅኝአዲስ	
18. አቶ ዩ ኬንስ መሾሀ ሰ ሙ	
19- አቶ ለመለ ፈጠነ	
20- አቶ ሙ ተሰማ ዓዓመ	

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህል፣ ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ

8.2. ለጥበቃ ሠራተኞች መኖሪያ ቤት መስሪያ የተመረጡ ቦታዎች

ተ.ቁ	የመኖሪያ ካምፑ ስም	የሚወስደው ጊዜ	የሚገኝበት ቀበሌ
1	ደዋርግ ዛና	2 ስዓት	ዓለ.
2	ማይጠበቆ	2 ስዓት	ዓለ.
3	ጮንቄ	2 ስዓት	ዓለ.
4	አዲመደባይ	2 ስዓት	ነብራ ፍድቃ
5	ወንድ ጋሬጣ	2 ስዓት	ነብራ ፍድቃ
6	ጅብ ዋሻ	2 ስዓት	ነብራ ፍድቃ
7	አጠላ/ጨውበር	2 ስዓት	ጨውበር
8	አዲሃ ወልውል	2 ስዓት	አዲአረጋይ
9	ምድማር	2 ስዓት	እንስያ/እንዞ መገናኛ
10	ማይፈዲን	2 ስዓት	በርማሪያም
11	ስቅማ	2 ስዓት	በርማሪያም

8.3. ጥበቅ ስፍራውን በአዋጅ ለማቋቋም የተመረጡ ጉልቶች

1. የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን ከምዕራብ አቅጣጫ ከሚያዋስነውና በሰሜን ጫፍ ከዓለ. ቀበሌ ድንበር የድቅቆና ዛሪማ ወንዞች ከሚገናኙበት ቦታ ከዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 38 ደቂቃ 14.8 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 46 ደቂቃ 48.6 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አንድን መነሻ በማድረግ፣
2. ከዚያም የዛሪማ ወንዝንና የኩመር አምቦ ተራራ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመቀጠል ከአርማደጋ ወደ ዛሪማ ወንዝ ከምትፈሰው የመቃብር ጥልቂት ሸለቆ አካባቢ በትይዩ ወንዙን ወደ ጥብቅ ስፍራው በማስገባት ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 37 ደቂቃ 31.4 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 47 ደቂቃ 0.6 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሁለት፣
3. ከዚያም የዛሪማ ወንዝንና የኩመር አምቦ ተራራ አካባቢን ተከትሎ በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል ከጎምባስ አየ መጨረሻ አካባቢ ወንዙን ወደ ጥብቅ ስፍራው በማስገባት ከወንዙ ዳርቻ ሰርኪን ዛፍ ላይ 13 ድግሪ 36 ደቂቃ 49.7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 47 ደቂቃ 16.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሶስት፣
4. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የግራር አምቦ ተራራ አካባቢን ተከትሎ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመቀጠል አምቦ ውሃ ጠበል ከሚገኝበት የወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 36 ደቂቃ 39 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 47 ደቂቃ 36.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አራት፣
5. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና መጋጮ አካባቢን ተከትሎ፤ ወንዙን ወደ ውስጥ በማስገባት ወደ ደበብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ከቀርነ አጋዘን ተራራ ስር መጋጮ መጨረሻ ከወንዙ ዳርቻ ከዲዛው ዛፍ ላይ 13 ድግሪ 35 ደቂቃ 21.3 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 47 ደቂቃ 23.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምስት፣
6. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የፋሲል ተራራ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመዞር በቀርነ አጋዘን ተራራ አካባቢ የፋሲል ተራራ ሽንጥሮና የዛሪማ ወንዝ ከሚገናኙበት ቦታ ትይዩ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 34 ደቂቃ 40.1 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 46 ደቂቃ 53 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስድስት፣
7. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የእንዳሞታይ ተራራ አካባቢን ተከትሎ በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል ቀርነማይ ተራራ አካባቢ ከደዋርግ ዛና መንደር ዝቅ ብሎ የገውሌ ሽንጥሮ እና የዛሪማ ወንዝ መገናኛ ከወንዙ ዳርቻ ሰርኪኑ ላይ 13 ድግሪ 33 ደቂቃ 47.9 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 46 ደቂቃ 35.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስባት፣
8. ከዚያም የዛሪማን ወንዝ ተከትለን ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር ደሳይ የመቃብር ቦታ ፊት ለፊት ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 32 ደቂቃ 55.7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 47 ደቂቃ 22.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ስምንት፣

9. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የእጣኖ መንደር የእርሻ ቦታዎችን ተከትሎ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ የመቃና ዛሪማ ወንዝ ከሚገናኙበት ቦታ ትይዩ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 31 ደቂቃ 49.5 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 48 ደቂቃ 14.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ዘጠኝ፣
10. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና ማይፃድቃን አካባቢ ተከትሎ በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል የእጣኖ መንደር የእርሻ ቦታ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ክርክራው ላይ 13 ድግሪ 31 ደቂቃ 39.6 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 48 ደቂቃ 46 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስር፣
11. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና ማይፃድቃን አካባቢ ተከትሎ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር ደብረንስሃ መንደር የእርሻ ቦታ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ከሰርኪኑ ላይ 13 ድግሪ 30 ደቂቃ 42.2 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 49 ደቂቃ 4.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አንድ፣
12. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የጓልዘሪማ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር የጓልዘሪማና ዛሪማ ወንዝ የሚገናኙበትን ቦታ አልፎ ማይጠበቆ መንደር ስር ወደ ዶቅማ ማቋረጫ መንገዱ አጠገብ ላይ 13 ድግሪ 29 ደቂቃ 48.7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 49 ደቂቃ 3 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሁለት፣
13. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የጓልዘሪማ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመቀጠል ማይመፍለስ አካባቢ ከሾላው ላይ 13 ድግሪ 29 ደቂቃ 32 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 48 ደቂቃ 58.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሶስት፣
14. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የገኖ አካባቢን ተከትሎ በዚያው ቅጣጫ በመቀጠል ዲማ መጨረሻ ከወንዙ ዳርቻ ዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 29 ደቂቃ 0.7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 49 ደቂቃ 1.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አራት፣
15. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የገኖ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር ጮንቄ የዳልሸሃ ኪዳነ ምህረት የአትክልት ቦታ አጠገቡ ላይ 13 ድግሪ 28 ደቂቃ 25.1 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 49 ደቂቃ 18.3 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ አምስት፣
16. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የገኖ አካባቢን ተከትለን በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል የአዲቅመንትዬ ሸለቆ እና ዛሪማ ከሚገናኙበት ሰርኪኑ ላይ 13 ድግሪ 27 ደቂቃ 49.3 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 49 ደቂቃ 21 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ስድስት፣
17. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የገኖ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመዞር የማይአንበሳ ሸለቆና ዛሪማ ከሚገናኙበት ወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 27 ደቂቃ 9.7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 49 ደቂቃ 13.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሰባት፣
18. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የማይአጋም አካባቢን ተከትሎ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመዞር የአዲሃምቡር ሸለቆና ዛሪማ የሚገናኙበትን ቦታ አልፎ ሰርኪኑ ላይ 13 ድግሪ 26 ደቂቃ 57 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 49 ደቂቃ 22.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ሰምንት፣
19. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የማይአጋም አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር የማይአጋም ሸለቆና ዛሪማ የሚገናኙበት ቦታ ትይዩ አዲሃምቡር አካባቢ ክርክራው ላይ 13 ድግሪ 26 ደቂቃ 39.7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 49 ደቂቃ 46.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አስራ ዘጠኝ፣
20. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የማይአጋም አካባቢን ተከትሎ በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል የአፍንጫ ድመ· ሸለቆና ዛሪማ የሚገናኙበት ቦታ ሰርኪኑ ላይ 13 ድግሪ 26 ደቂቃ 23.4 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 49 ደቂቃ 42.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ፣
21. የዛሪማን ወንዝና የማይአጋም አካባቢን በመከተል ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ ዳልሻሃ ኪ/ምህረት ገዳም አካባቢ የዓለ ቀበሌንና የሳንቅ ቀበሌን ከሚያዋስነው ሳሙ·ኤል ቤ/ክርስቲያን የሳሙ·ኤል ሸለቆና ዛሪማ ከሚገናኙበት ቦታ ከወንዙ ዳርቻ ኩመር ዛፍ ላይ 13 ድግሪ 26 ደቂቃ 2.7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 49 ደቂቃ 56.3 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ አንድ፣
22. የዛሪማን ወንዝና የማይአጋም አካባቢን በመከተል ከዚያም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ዳልሻሃ ኪ/ምህረት ገዳም አካባቢ የሳንቅ ቀበሌንና የነብራፍድቃ ቀበሌን ከሚያዋስነው የጠረኩ ሸለቆና ዛሪማ ከሚገናኙበት ቦታ ከድልድዩ ዝቅ ብሎ ወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 59.8 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 50 ደቂቃ 2.6 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ ሁለት፣
23. የዛሪማን ወንዝና የማይአጋም አካባቢን በመከተል ከዚያም ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የዳልሻሃ ኪ/ምህረት ገዳም የእናቶች እርሻና ቅራት መጠበቂያ አዲባሮ አካባቢ የማይጨርጨሪትና አዲባሮ ሸለቆዎች ከዛሪማ ወንዝ የሚገናኙበት ቦታ ከወንዙ ዳርቻ ዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 53.8 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 50 ደቂቃ 22 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ ሶስት፣

24. የዛሪማን ወንዝና የማይአጋም አካባቢን በመከተል ከዚያም ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመታጠፍ የዳልሻሃ ኪ/ምህረት ገዳም የአባቶች እርሻ ጎሜ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ሰርኪኑ ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 58.6 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 50 ደቂቃ 38.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ አራት፣
25. የዛሪማን ወንዝና የማይአጋም አካባቢን በመከተል ከዚያም በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል የዳልሻሃ ኪ/ምህረት ገዳም የአባቶች እርሻ ጎሜ አካባቢ ከስፍራ አባነብሮ ትይዩ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 26 ደቂቃ 9.3 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 50 ደቂቃ 51.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ አምስት፣
26. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የማይአጋም አካባቢን ተከትሎ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የዳልሻሃ ኪ/ምህረት ገዳም የአባቶች እርሻ ስድስት ምንጮች (አቡነ አረጋይ፣ ራጉኤል፣ ባታ፣ አቡዬ፣ መድሃኒያለምና ኪዳነ ምህረት) ከሚገኙበት የአምቦ ጠበል አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ሰርኪኑ ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 56.5 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 51 ደቂቃ 39.3 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ ስድስት፣
27. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የወልማማ ጠማማ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ የዳልሻሃ ኪ/ምህረት ገዳም የእባቶች እርሻ ጥቁር ባህር አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 46.2 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 51 ደቂቃ 39.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ ሰባት፣
28. ከዚያም የዛሪማን ወንዝና የወልማማ ጠማማ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የዳልሻሃ ኪ/ምህረት ገዳም የአባቶች እርሻ ዘቅዘቁ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ክርክራው ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 22.1 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 51 ደቂቃ 50.3 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ ስምንት፣
29. ከዚያም የወልማማ ጠማማ አካባቢን ተከትሎ የዛሪማ ወንዝ ደኑን ከሚያዋስንበት መጨረሻ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ የዳልሻሃ ኪ/ምህረት ገዳም የአባቶች እርሻን ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመተው ሙሽራ መቃብር አካባቢ የአብዬ ወንዝና ዛሪማ ከሚገናኙበት ቦታ ትይዩ ከወንዙ ዳርቻ ዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 20.4 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 52 ደቂቃ 1.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃያ ዘጠኝ፣
30. ከዚያም አብዬ ወንዝንና የወልማማ ጠማማ አካባቢን ተከትሎ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመዞር የሰቋር ኪ/ምህረት ገዳም የአባቶች እርሻና ቅራት ቦታ ወንድ ጋራጣ አካባቢ ከቅንጭብ ሸለቆ አጠገብ ከወንዙ ዳርቻ ሾላውና ዋርካው ከተጣበቁበት ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 25.1 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 52 ደቂቃ 17 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ፣
31. ከዚያም አብዬ ወንዝንና የወልማማ ጠማማ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር ወንድ ጋራጣ ጎጥ ማይጠሰሶ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ገመሮው ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 16.7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 52 ደቂቃ 37.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ አንድ፣
32. ከዚያም አብዬ ወንዝንና የማይሱር አካባቢን ተከትሎ ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር ወንድ ጋራጣ ጎጥ ማይጠሰሶ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 25.2 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 53 ደቂቃ 0.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ ሁለት፣
33. ከዚያም አብዬ ወንዝንና የድብድብ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር ወንድ ጋራጣ ጎጥ ማይጠሰሶ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ሰርኪኑ ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 14.7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 53 ደቂቃ 11.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ ሶስት፣
34. ከዚያም አብዬ ወንዝንና የድብድብ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመዞር ወንድ ጋራጣ ጎጥ ማይጠሰሶ አካባቢን ወደ ሰሜን ምዕራብ በመተው አዲጎላ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 24 ደቂቃ 43.4 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 53 ደቂቃ 10.6 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ አራት፣
35. የድብድብ አካባቢን በመተው ከዚያም የአብዬ ወንዝንና ከእንዳሚካኤል ተራ ዝቅ ብሎ የሞላላ ሜዳ አካባቢን ተከትሎ ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር አዲጎላ አካባቢ የጎምባር ሸለቆን አልፎ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 1.2 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 53 ደቂቃ 34.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ አምስት፣
36. ሞላላ ሜዳን በመተው ከዚያም የአብዬ ወንዝንና የእንዳሚካኤል ተራ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመዞር አዲጎላ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 24 ደቂቃ 11.4 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 54 ደቂቃ 1.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ ስድስት፣
37. ከዚያም የአብዬ ወንዝንና የእንዳሚካኤል ተራ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ ጅብ ዋሻ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 23 ደቂቃ 52.9 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 54 ደቂቃ 3.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ ሰባት፣

38. ከዚያም የአብዬ ወንዝንና የእንዳሚካኤል ተራ አካባቢን ተከትሎ በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል ጅብ ዋሻ አካባቢ ካለው መስክ አጠገብ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 23 ደቂቃ 49.8 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 54 ደቂቃ 35.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ ስምንት፣
39. የእንዳሚካኤል ተራን በመተው ከዚያም የአብዬ ወንዝን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ የሰቋር ኪ/ምህረት ገዳም ሸለቆና የአብዬ ወንዝ ከሚገናኙበት ቦታ ትይዩ ጅብ ዋሻ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 23 ደቂቃ 34.9 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 54 ደቂቃ 53.9 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሰላሳ ዘጠኝ፣
40. የጅብ ዋሻ አካባቢን በመተው ከዚያም የአብዬ ወንዝንና የሰቋር ኪ/ምህረት ገዳም አካባቢን ተከትሎ ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመዞር ማይደንጎላ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 23 ደቂቃ 32.1 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 54 ደቂቃ 48.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ፣
41. የማይደንጎላ ወንዝንና አካባቢውን ወደ ምዕራብ በመተው ከዚያም የአብዬ ወንዝንና የሰቋር ኪ/ምህረት ገዳም አካባቢን ተከትሎ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር የማይደንጎላ ወንዝና የአብዬ ወንዝ ከሚገናኙበት ከሰቋር ጊዮርጊስ ቤ/ክርስቲያን ጫፍ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 23 ደቂቃ 22.6 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 55 ደቂቃ 5.3 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ አንድ፣
42. ሰቋር ኪ/ምህረት ገዳምን በመተው ከዚያም የአብዬ ወንዝንና የሰቋር መድሃኒያለም ቤ/ክርስቲን አካባቢን ተከትሎ ወደ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር ሰቋር ጊዮርጊስ ቤ/ክርስቲያን አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 23 ደቂቃ 23.2 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 55 ደቂቃ 20.7 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ ሁለት፣
43. የሰቋር መድሃኒያለም ቤ/ክርስቲን አካባቢን በመተው የአብዬ ወንዝንና ነደላ አምባን ተከትሎ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር የነደላ አምባን ከሰቋር መድሃኒያለም ቤ/ክርስቲን አካባቢ ከምትለየው ሸለቆ ፊት ለፊት ሰቋር ጊዮርጊስ ቤ/ክርስቲያን አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 23 ደቂቃ 15.4 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 55 ደቂቃ 43.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ ሶስት፣
44. የሰቋር ጊዮርጊስ ቤ/ክርስቲን አካባቢን በመተው የአብዬ ወንዝንና ነደላ አምባን ተከትሎ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመዞር ሽልዋ አካባቢ ጫፍ ከወንዙ ዳርቻ ዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 23 ደቂቃ 5.7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 55 ደቂቃ 44.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ አራት፣
45. የአብዬ ወንዝን በመተው ከዚያም ነደላ አምባን ተከትሎ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመዞር የአብዬ ወንዝን ከሚፈጥሩትና ራስ ከሆኑት ሁለቱ የሽልዋ ሸለቆዎች ከሚገናኙበት ቦታ ዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 22 ደቂቃ 59 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 55 ደቂቃ 50.9 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ አምስት፣
46. የሽልዋ መንደሮችን አርሻ ወደ ምስራቅ ነደላ አምባን ወደ ምዕራብ በመተው ደኑን አያካለለ የሚፈሰውን አንደኛውን የሽልዋ ሸለቆ እና ነደላ አምባን ተከትሎ ወደ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በመዞር የነብራ ፍድቃ ቀበሌንና የጨውበር ቀበሌን ከሚያዋስነው ነደላ አምባ ገደሉ ስር ከሽልዋ ሸለቆ መጨረሻ ላይ 13 ድግሪ 23 ደቂቃ 16.5 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 56 ደቂቃ 33.2 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ ስድስት፣
47. የእንዞ ወንዝንና የገውሌ ዱር አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ የበርማሪያም ቀበሌንና የጨው በር ቀበሌን ከሚያዋስነው የማይሸሃ ወንዝና እንዞ ከሚገናኙበት ቦታ ትይዩ ከወንዙ ዳርቻ ዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 23 ደቂቃ 44.6 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 58 ደቂቃ 35.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃምሳ ስምንትን ዞሮ የነብራ ፍድቃ ቀበሌንና የጨውበር ቀበሌን ከሚያዋስነው ጉልት ቁጥር አርባ ሰባት፣
48. የማይፈዲ አካባቢን በመተው ከዚያም የእንዞ ወንዝንና የገውሌ ዱር አካባቢን ተከትሎ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ በመታጠፍ የማይፈዲና የስቅማ አካባቢዎችን ከሚለየው የስቅማ ሸለቆ የስቅማ ጎጥ አካባቢ መነሻ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 5.6 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 58 ደቂቃ 35.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ ስምንት፣
49. የጊዮርጊስ ተራን በመተው ከዚያም የእንዞ ወንዝንና የገውሌ ዱር አካባቢን ተከትሎ በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል የገውሌ ዱር አካባቢንና የጊዮርጊስ ተራን ከሚለየው ከገውሌ ዱር ሸለቆ ትይዩ ማይፈዲ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 25 ደቂቃ 15 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 58 ደቂቃ 30.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አርባ ዘጠኝ፣
50. የማይሸመሎ አካባቢን በመተው ከዚያም የእንዞ ወንዝንና የጊዮርጊስ ተራን ተከትሎ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ የሰቋር ኪዳነ ምህረት ገዳም የአባቶች እርሻና ቅራት አጠገብ ማይፈዲ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 26 ደቂቃ 28.4 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 58 ደቂቃ 25.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃምሳ፣

51. የሰፊ ጭንጫን አካባቢ በመተው ከዚያም የእንዞ ወንዝንና የጊዮርጊስ ተራን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ የሰፊ ጭንጫንና የጊዮርጊስ ተራ አካባቢን ከሚለየው ከሰፊ ጭንጫ ወንዝ ትይዩ ማይሸመሎ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 26 ደቂቃ 53.1 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 58 ደቂቃ 11.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃምሳ አንድ፣
52. የአይጠየፍንና እንጥልጥሌ አካባቢዎችን በመተው ከዚያም የእንዞ ወንዝንና ሰፊ ጭንጫ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመዞር ማይሸመሎ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 27 ደቂቃ 31.7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 58 ደቂቃ 8.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃምሳ ሁለት፣
53. የሩብሱርባ አካባቢን በመተው ከዚያም የእንዞ ወንዝንና የአይጠየፍ አካባቢን ተከትሎ በዚያው አቅጣጫ በመቀጠል ከአይጠየፍ መካነ መቃብር አካባቢ ትይዩ እንጥልጥሌ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 27 ደቂቃ 50.2 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 58 ደቂቃ 5.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃምሳ ሶስት፣
54. ከዚያም የእንዞ ወንዝንና የሩብሱርባ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ በመታጠፍ የማይልሃምንና የሩብሱርባ አካባቢን ከሚለየው የሩብሱርባ ሸለቆ ትይዩ እንጥልጥሌ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 28 ደቂቃ 16.9 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 57 ደቂቃ 51.5 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃምሳ አራት፣
55. የአዲሃወልውል ጎጥንና የእንስያ ወንዝን ወደ ሰሜንና ምስራቅ አቅጣጫ በመተው ከዚያም የማይልሃም አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ አቅጣጫ በመታጠፍ የአዲአረጋይ ቀበሌንና የበርማሪያም ቀበሌን ከሚያዋስነው የእንስያ ወንዝና የእንዞ ወንዝ ከሚገናኙበት ምድማር አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ላይ 13 ድግሪ 28 ደቂቃ 24.5 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 57 ደቂቃ 51.8 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር ሃምሳ አምስት፣
56. ችብሃ ወንዝን በመተው ከዚያም የእንስያ ወንዝና የማይልሃም አካባቢን ተከትሎ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመዞር አዲሃወልውል ጎጥ የችብሃ ወንዝና የማይልሃም አካባቢን ከሚለየው የአብዬ ሸለቆ ትይዩ ከወንዙ ዳርቻ ዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 28 ደቂቃ 57.3 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 57 ደቂቃ 49.1 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ ስድስት፣
57. ከዚያም የእንስያ ወንዝና የችብሃ ወንዝ አካባቢን ተከትሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በመቀጥል አዲሃወልውል ጎጥ አሸዋ ወንዝ አካባቢ ከወንዙ ዳርቻ ዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 29 ደቂቃ 7 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 57 ደቂቃ 50 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ ሰባት፣
58. ይህን አቅጣጫ በመቀየር የማህበረሰብ ጥብቅ ስፍራውን ከምስራቅ አቅጣጫ ከሚያዋስነውና በሰሜን ጫፍ የአዲአረጋይ ቀበሌንና አዲወፋሪ ቀበሌን ከሚለየው የማይቆላ ሸለቆ የአዲሃወልውል ጎጥ ጫፍ እንስያ ወንዝ ዳርቻ ከዓለቱ ላይ 13 ድግሪ 29 ደቂቃ 52.3 ሴኮንድ ሰሜንና በ37 ድግሪ 57 ደቂቃ 28.4 ሴኮንድ ምስራቅ ጉልት ቁጥር አምሳ ስምንት፣

8.4. በወረዳና በቀበሌ ደረጃ የፀደቀ የአዋሳኝ ቀበሌዎች የድንበር ወሰን መረጃ

GPS Coordinates of Armadega Natural Forest Proposed Protected Area Boundaries (Zone 37 Map Datum Adindan)

Id.	X -coordinate	Y-coordinate	Altitude	Station (Point) Name	Kebele	Direction From Previos Piont	Remark/Beacons
001	368053	1507825	852	Dikiko- Zarima rivers Megenagna	Ali	North on stone	B1
